# ምዕራፍ ፯
# የኢትዮጵያ ህልውና፡ ባንዳነትና ስደተኛነት



ራስ ደስታ ዳምጠውን ባንዳው ይዞ ለግድያ ሲወስዳቸው

## ስደተኝነት

ባንዳነት የኢትዮጵያን ህልውና እንደሚፈታተን ሁሉ ስደተኛነትም የኢትዮጵያን ህልውና ይፈትናል፤ ልዩነቱ ባንዳነት ኢትዮጵያን ለማፈራረስና ለማጥፋት የሚፈልግ ሲሆን ስደተኛነት በዓላማም ይሁን በተግባር ኢትዮጵያን የማጥፋት አቅዋም የለውም፤ ግን የኢትዮጵያን ህልውና የሚያሳሳ መሆኑ የማይካድ ሐቅ ነው፤ ውሎ አድሮ ልማድ ሲሆን ግን ስደተኛነት የኢትዮጵያ





ህልውና እያሳሳ አካላዊ ጉልበትም፣ የአእምሮ ክህሎትም፣ መንፈሳዊ ወኔም እየቀነሰ ሲሄድ የኢትዮጵያን ህልውና አደጋ ላይ እንደሚጥለው አያጠራጥርም፤ ከማናቸውም ጊዜ የበለጠ ዛሬ ብዙ ኢትዮጵያውያን ሴት-ወንድ ሳይል በኢትዮጵያ ውስጥ ከመኖር ይልቅ የስደትን ኑሮ የመረጡበት ጊዜ ነው፤ ሌላው ቀርቶ ትልልቅ ከተሞችን አይተው የማያውቁ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ የባላገር ሴቶች የቤት ሠራተኞች ለመሆን በየአረብ አገሩ አውሮጳላኖችን እየሞሉ ሲሄዱ ማየት የተለመደ የዕለት-ተዕለት ትዕንት እየሆነ ነው።

ምናልባት ከስደተኞች ሁሉ ኢትዮጵያን የጎዳው የቤተ እሥራኤሎች ነው፤ የቤተ እሥራኤሎች ስደት፣ ሙልጭ ብሎ ከኢትዮጵያ መውጣት ኢትዮጵያን ምን ያህል እንዳራቆታት እስካሁን ማንም አልተረዳም፤ ተከታታይ የኢትዮጵያ አገዛዞች ገና አልገባቸውም፤ ቤተ እሥራኤሎችም አልተረዱትም፤ ቤተ እሥራኤሎች በሃይማኖት ልዩነት ምክንያት በክርስቲያኖች ወገኖቻቸው የሚደርስባቸው ንቀትና ማግለል ለከፋ ስደት እንደዳረጋቸው ገና አልተገነዘቡም፤ በነጮች ይሁዲዎች በእሥራኤል የሚደርስባቸው በደል በጣም የከፋና የማይችሉት ይሆናል።

የቤተ እሥራኤል መሰደድ የኢትዮጵያን የታሪክ መሠረት፣ ከንግሥተ ሳባና ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ ያለውን የቅድመ ክርስትና የኢትዮጵያ ታሪክ ደምስሶና ባዶ አድርጎ አድርጎ አስቀርቶታል፤ በኋላ ቀዳማዊ ምኒልክ የተባለው የሰሎሞንና የሳባ ልጅ አባቱን ለመጎብኘት በሄደበት ጊዜ ንጉሥ ሰሎሞን ‹አንተ በዙፋኔ ላይ ትቀመጣለህ፤ በእኔ ፋንታም ትነግሣለህ፤›› ሲለው የያኔው ኩሩ አበሻ ‹‹ጌታዬ ሆይ እናቴንና አገሬን እተው ዘንድ አይቻለኝም፤ ...›› የሚል መልስ ሰጠና ወደአገሩ ተመለሰ፤ የዛሬዎቹ ቤተ እሥራኤሎች እናትም፣ አገርም ሌላ አለን ብለው በአውሮጳላን ሄዱ።

*ከኢጣልያ ወረራ በኋላ፣ በተለይም በደርግና በወያኔ* የአገዛዝ ዘመኖች ኢትዮጵያውያን በስደት የታወቁ ሆነዋል፤ ዛሬ በየትኛውም አህጉር ባሉ አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያውያን



ራስ ደስታ ዳምጠውን ባንዳው ይዞ ለግድያ ሲወስዳቸው

በስደተኛነት ያልገቡበት አገር ያለ አይመስለኝም፤ ምናልባት እንደኢትዮጵያውያን አገሩን የሚወድ ሕዝብ የለም ይሆናል፤ ያም ሆኖ ስደተኛነት የኢትዮጵያውያን አማራጭ ኑሮ ሆኖአል፤ የዘንድሮው አዳፍኔ አገሪቱን እሾህ በእሾህ አድርጎ መቆሚያ መቀመጫ በማሳጣቱ አገሪቱ ለኢትዮጵያ ወጣት የማትመች ሆናለች፤

ስደት ከዋናዎቹ የመክሸፍ መገለጫዎች አንዱ ነው፤ ስደት ሽሽት ነው፤ ሽሽት የፍርሃት ክንፍ ነው፤ በሕይወት ላይ፣ በነፍስ ላይ አደጋ ሲዘነዘር፣ በሌሎች ላይ ያዩት አበሳና መከራ ወደራስ እየቀረበ ሲመጣ የተካበው ተስፋ ሁሉ ተንኮታኩቶ ሕይወትና ኑሮ ባዶ ጨለማ ሲሆንበት፣ የኋለውንም ሆነ የፊቱንም ሳይመለከት፣ መነሻውንና መድረሻውን ሳያመዛዝን እግሩን ተከትሎ ወደሚደርስበት መሄድ ነው፤ በኢትዮጵያ ስደት የመክሸፍ መገለጫ መሆኑን ለመረዳት ስደትን ከባንዳነት ጋር ማነጻጸር ነው፤ ስደተኛነትንና ባንዳነትን በሰፊው ያቀራረቡ ምናልባት አጼ ኃይለ ሥላሴ ሳይሆኑ አይቀሩም፤ የእሳቸውን መሰደድ ብዙ መኳንንት አልወደዱትም ነበርና ስደት ለሳቸው ቁስል ነበር፤

እንደደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ያሉ ከጊዜያቸው ቀድመው የተራመዱ ነበሩና ከእነዚህ ለመከላከል አጼ ኃይለ ሥላሴ ከባንዶች ጋር መቧደን ሳያስፈልጋቸው አልቀረም ይሆናል፤ ባንዶች በኢጣልያ አሽከርነታቸው ያገኙት ሥልጣናም እንደሚያገለግላቸው ሳይገምቱ አልቀሩም ይሆናል።

በመጀመሪያው ላይ እንደገለጽሁት በኢትዮጵያ ታሪክ መክሸፍ ያልታየበት አንድነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ህልውና ነው፤ ምናልባትም በሃያኛው ምዕተ-ዓመት ኢትዮጵያን ያጋጠማት ፈተና የፋሺስት ኢጣልያ የኢትዮጵያን ህልውና ለመጀመሪያ ጊዜ በምር የፈተነበትና አርበኝነትን የፈጠረበት መሆኑ ይመስለኛል፤ የኢትዮጵያን ህልውናና አርበኝነትን አጣምረን በአንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ባንዳነትንና ስደተኛነትን አነጻጽረን ማየት የምንገደድበት የታሪክ ሁኔታ ውስጥ ገብተናል፤ የኢትዮጵያን የረጅም ጊዜ ታሪክ ልዩና እኩሪ የሚያደርገውንና ያልከሸፈውን የኢትዮጵያን ህልውና ለማስከበር የተፈጸመው ተጋድሎ አርበኝነት





ነው፤ አርበኝነት የኢትዮጵያን እኩሪ ታሪክ ለማስቀጠልና የአባቶቻቸውን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ የተደረገ የቆራጥ ዜጎች የሞት-ሽረት ትግል ነው፤ በአንጻሩ ባንዳነትና ስደተኛነት የመክሸፍ መገለጫዎች ይሆናሉ።

## ባንዳነት ወይም ለኢጣልያ መገበር

የአቡነ ጴጥሮስ ደም ሳይደርቅ ሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስ፣ እጬጌ፣ ንቡረ ዕድ የፋሺስት ሎሌዎች ሆነው በአንድ ድምጽ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፋሺስት ኢጣልያ በሰላም እንዲገዛ ሲሰብኩ ብሔራዊ መክሸፍ ፍጹም የሆነ ይመስላል።

እንግዲህ ሌላ ሌላው በገንዘብ እየተገዛ ኢጣልያንን ቢያገለግል ምንም አያስደንቅም፤ ራስ ደስታ ዳምጠውን ይዞ ለኢጣልያ ያስረከበው ‹‹የትግሬው ደጃዝማች ትክሉ መሸሻ ነው፤ **ደጃዝማቹ ለፈጸመው ጀብዱ 20000 ሊሬ፣ የብር ልሻን፣ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት ኮከብ የሚል ሽልማትም አግኝቷል።››**[51]

አንዱና ዋናው የአገር ምሰሶ የነበረውና በትረ መንግሥቱን የጨበጠው ንጉሠ ነገሥት ሸሽቶ ሲሰደድ፣ ሁለተኛውና ዋናው የአገር ምሰሶ የነበረው፤ ጴጥሮስ በመትረየስ ተደብድቦ ሲሞት የተተካው ሊቀ ጳጳስ ‹‹ለሙሶሊኒ ተገዙ›› እያለ ሲሰብክ ለኢትዮጵያ የቆሙላት በዱርና በገደሉ ተሰማርተው ሰንደቅ ዓላማዋን እያውለበለቡ የሚዋደቁላት አርበኞች ብቻ ነበሩ፤ ቆይቶ ግን ስደተኛው ንጉሠ ነገሥት ከተመለሱና ሥልጣናቸውን ከአደላደሉ በኋላ አብዛኛዎቹ አርበኞች ኩራታቸውንና ክብራቸውን ተገፈው ሥልጣን ሁሉ ለባንዶችና ለስደተኞች ሆነ።

መንፈሳቸውን ያፈረጠሙ እስከመጨረሻው በአልበገር-ባይነት ሲገፉ የሚያወላውሉት ለኢጣልያ እጃቸውን እየሰጡ ይገደላሉ፤ ለምሳሌ ደጃዝማች አበራ ካሣ ከወንድማቸው ጋር እጅ ሰጥተው ታረዱ፤[52] በአጠቃላይ ሲታይ መሳፍንቱና መኳንንቱ

[51] Alberto Sbacchi, Ethiopia Under Mussolini, p. 189

[52] ጳውሎስ ኞኞ፣ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት፣ አዲስ አበባ፣ 1980.

የመዋጋት ዝንባሌ አልነበራቸውም፤ የታወቁት ራሶች ሁሉ ለኢጣልያ ገብረዋል፤ አቶ ተድላ ዘዮሐንስ እንደሚለው -

**‹‹ጣልያን አዲስ አበባ እንደገባ ከሀድያን በዙሪያው ተኮለኮሉ፤ ስድስት ራሶች፣ አንድ ጳጳስ፣ ሦስት ሡልጣኖች፣ አንድ ሼህ፣ አራት ደጃዝማቾች ያላንዳች ችግር ገቡለት፤በየአደባባዩ እያቆመ ቃላቸውን በመሐላ ተቀበላቸው፤አስፈረማቸው፤ ደመወዛቸውንም እንደአገልግሎታቸው እያየ ቆረጠላቸው፤ ከፍተኛ ደመወዝ የዋና ታማኙ የራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት፣ ትንሹ ደግሞ የደጃዝማች ታየ ጉልላት ነበር።[53]**

ከንጉሠ ነገሥቱ ስደት ጋር ሲታይ ሥርዓቱ የፈረሰው ከላይ እንደሆነ ያረጋግጣል፤ አቶ ተድላ ሌሎች ከሀዲዎችንም ይጠቅሳል፤-

**ደጃዝማች መሸሻ ተወንድ በላይ በጅሩ፣ ደጃዝማች ማሞ ኃይለ ሚካኤል በጎጃም፣ ደጃዝማች ሀብተ ማርያም በነቀምት፣ አባ ጆቢር አባ ጅፋር በጂማ፣ ደጃዝማች ዓመዴ በወሎ፣ ደጃዝማች አያሌው ብሩና እናዛዡ መነኩሴ አባ ተክለ ማርያም በጎንደር፣ ፊታውራሪ ተሰማ ከተማ በቡልጋ፣ ወሩ በላይነህና አሊ ኡመር በበረከት ፊታውራሪ ሣህሉ ወልደ ገብርኤል በመንዝ፣ አቶ አበበ ዘገኑና አቶ ሰሙ በደብረ ብርሃን፣ በመርሐቤቴ ደግሞ ንዳው ጭንቅሎ፣ አፈቄሣር አፈወርቅ ሳይጠቀሱ አይታለፉም።››[54]**

እነዚህ ሰዎች የፈጸሙትንም የክህደት ተግባር ይዘረዝራል፤ ከነዚህም ጥቂቶቹን መጥቀስ ግዴታ ሆኖ ይታየኛል፤--

**መሳፍንቱና መኳንንቱ ለጠላት ምሥጢር በማቀበል ... የከዱት ጳጳሳት በመገዘት ... ራሳቸውን ለጣልያን ጦር፣ በተለይም ለባንዳው በመሪነት እየቆሙ ያዋጉ ብዙዎች ናቸው፤ በጣልያን**

[53] ዝኒ ከማሁ፤ ገ. 389.

[54] ዝኒ ከማሁ





**አደባባይ ላይ እየተቀመጡ አርበኛ ተይዞ በቀረበ ጊዜ ፍርድ እያከበዱ ያስገደሉ አያሌ ናቸው፤ እንዲህ የሚያደርጉት ለጌታቸው ያላቸውን ታማኝነት በግብር ለማረጋገጥ ነበር፤››[55]**

በአጠቃላይ ሲታይ ‹‹የንጉሠ ነገሥቱ ሹማምንቶች፣ ባለሙዋሎች ከጣልያን ጎን ቆሙ፤ ለሀገሪቱዋ የተዋጉላት የሞቱላት በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ሞገስ አጥተው የታሰሩ፣ የተገረፉ ሆኑ፤ ለአብነት ደጃዝማች አውራሪስ ዱሉ፣ ደጃዝማች ባልቻና ደጃዝማች በየነም ይጠቀሳሉ፤ ...››[56]

**ሰንጠረዥ 4**
**ከኢጣልያ መንግሥት ደመወዝ ተቀባዮች**
**መሳፍንትና መኳንንት**

| ስም | ደመወዝ |
|---|---|
| ራስ ኃይሉ | 40874 |
| ራስ ሥዩም | 22900 |
| ራስ ጉግሳ | 25000 |
| ራስ ጌታቸው | 7000 |
| የአውሳ ሱ. መሀመድ እንፋሪ | 15000 |
| ሱልጣን አብዱላሂ አባ ጂፋር | 8000 |
| ሱልጣን አባ ጆቢር አብዱላ | 8000 |
| ደጃዝማች ሆሳእና ጆቴ | 15000 |
| ደጃዝማች ዮሐንስ ጆቴ | 15000 |
| ሼክ ኤል ሆጀሌ | 25000 |
| ደጃዝማች ታየ | 1000 |
| ራስ እምሩ | 1000 |
| ደጃዝማች አያሌው ብሩ | 16000 |

ምንጭ፡- Alberto Sbacchi[57]

ይህንን ሀሳብ ለመወነጃጀል መጠቀሚያ ማድረግ ለወደፊቱ ታሪክ ሊሰጥ የሚችለውን አገልግሎት በጣም ይቀንሰዋል፤ በኢትዮጵያ የሩቅም ሆነ የቅርብ ታሪክ ዜጎችን ሁሉ የሚያኮራው

[55] ዝኒ ከማሁ፤ ገ. 390.

[56] ዝኒ ከማሁ፤ ገ. 393.

[57] Alberto Sbacchi,

ሁነት ኢትዮጵያውያን የአገራቸውን ህልውና ለማስከበር ሁሌም ያደረጉት ተጋድሎና አልበገር-ባይነት ነው፤ መክሸፍ ያልነካው የጸዳ ታሪክ ነው፤ ይህ የጸዳ ታሪክ ከ1928 የኢጣልያ ወረራ ወዲህ እየደፈረሰ ነው፤ ይህንን ጉዳይ ሳንነጋገርበትና ሳንከራከርበት እንዲሁ እንደደራሽ ጎርፍ ይዞን ሲሄድና እያጎደፈ ሲለውጠን በዝምታ መቀበሉ ሰው መሆናችንን ጥያቄ ውስጥ ያስገባዋል፤ ስለዚህ ነው በአርበኝነት፣ በስደተኝነትና በባንዳነት ላይ በትንሹም ቢሆን ልንነጋገርባቸው የሚገባን።

ለኢጣልያ ከገበሩ መሳፍንትና መኳንንት መሀከል ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ዋናው ናቸው፤ በወር ደመወዛቸው ከለካነው ራስ ኃይሉ የሁለቱን የራስ ሥዩምንና የራስ ጉግሳን ያህል ያገኛሉ፤ ይህ የሆነበትን ምክንያት ለማወቅ ብዙ መላ-ምት ውስጥ የሚያስገባ በመሆኑ እተወዋለሁ፤ ነገር ግን እንዚህ መሳፍንት በየአካባቢያቸው በኢጣልያ ዘመን ከነበረው የጸጥታ ሁኔታ ጋር ማገናዘብ ሳያስፈልግ እንደማይቀር ማሳሰብ ያስፈልጋል፤ የመሳፍንቱና የመኳንንቱ ለኢጣልያ መገበር የቆየ መሆኑን ዝባ[illegible] የሚባለው የኢጣልያ ምሁር ፍንጭ ይሰጣል፤ ራስ ጌታቸው ሲታሰሩ አስቀድመው ለኢጣልያ መገበራቸን ገልጸው ኢጣልያኖች ቃላቸውን እንዳላከበሩላቸው በመውቀስ ለግራዚያኒ ደብዳቤ ጽፈዋል፤ ራስ ሥየምም ሁልጊ[illegible]ም ለኢጣልያ ታማኝ እንደነበሩ በራሳቸው፣ በራስ ከበደና በደ[illegible]ማች ዓሥራት ስም ጽፈዋል።[58]

ባንዳነት ከጎሣ ጋር መያያዙን ፋሺስት ኢጣልያ እንደጀመረውና እንደተጠቀመበት በሰንጠረጅ ሦስትና አራት ምልክትን የምናገኝ ይመስለኛል፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከፋፍሎ ለመግዛት ጎሣ በመሣሪያነት አገለገለ፤ ሰንጠረጅ 3ና ሰንጠረጅ 4 ማስረጃ ይሆናሉ፤ ይህ ትምህርት ሆኖ ዛሬም እያገለገለ ነው፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተበረከተው አዲሱ ጎሣ ቅማንት ነው።

መነጋገሪያችን መክሸፍ ያላጋጠመው የኢትዮጵያ ህልውና ነው፤ ጎሠኝነትና ባንዳነት የኢትዮጵያን ህልውና ለሚፈታተኑ

[58] Alberto Sbacchi, *Legacy of Bitterness, Ethiopia and Fascist Italy,1935-1941*, Asmara, 1997, p. 131.





ኃይሎች በመሣሪያነት የሚያገለግሉ መሆናቸውን መገንዘብ አለብን፤ ልንገነዘበው የሚገባን አንድ ሌላ ነገር አለ፤ ፋሺስት ኢጣልያ በጎሣ ልዩነት በሌሎቹ የኢትዮጵያ ክፍሎች የተጠቀመበትን ያህል በኤርትራ ውስጥ አልተጠቀመበትም፤ በኤርትራ የከፋፍለህ ግዛ ዋና መሣሪያ ያደረገው ሃይማኖትን ነበር።

**ሰንጠረጅ 5**
**ከኢጣልያ መንግሥት ደመወዝ ተቀባዮች**
**የሀረር ሹማምንት**

| የሹሞች ስም | ደመወዝ |
|---|---|
| አለቃ ደስታ ነገዎ አማካሪ* | 1087 |
| ሱፊያን አሚር አብዱላ የአደሬዎች ሹም | 1200 |
| ግዛው ከተማ የአማሮች ሹም | 1200 |
| ጃሲም ቤን ዩሱፍ የሶማሌ | 700 |
| አማር አሊ አብዱላ የኦሮሞ ከምቦልቻ | 550 |
| ኃይሌ ማራኑ የከምቦልቻ አማራ | 866 |
| ደሰታ ዳምጠው የግራዋ አማራ | 866 |
| ደመቀ ኡበሬ የሞጆ አማራ | 400 |
| ዋዝ አሳን ኤርዚ የኢሳ | 200 |
| ዝቸታ ወልዳጃ የአማራ ሹም በጨርጨር | 1200 |
| ሚልዮን ተድላ የጨርጨር አማራ ሹም | 3333 |
| አደን አበዲ ሳቡር የኦሮሞ በደደር | 1166 |
| ሀሜል ገመዳ ጢቾ አርሲ | 550 |
| ቁሪ ቁላ አርሲ ኮሮሌ | 500 |
| ኑሀ ዳዲ የጊኒር ሹም | 1639 |
| ሰይድ መሀመድ የሼክ ሁሴን ኢማም | 1100 |

ምንጭ፡- Alberto Sbacchi፣ ገ.154
*የነገብረ ክርስቶስ ደስታ አባት ናቸው፤ አለቃ ደስታ ነገዎ

ፋሺስት ኢጣልያ ጎሣንና ሃያይማኖትን መሣሪያ አድርጎ የኢትዮጵያን ሕዝብ ቢያዳክምም፣ ሹሞቹንና አለቃዎቹን በገንዘብ እየገዛ ቢደልልም፣ አብዛኛው ሕዝብ



በትግራይ የነበረው ዋና ባንዳ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ

አልተበገረለትም፤ ለዚህም ዋናውና ተጨባጭ የሆነው ማስረጃ ለጎጃሙ ራስ ኃይሉ ሲከፍል የነበረው ገንዘብና በጎጃም የነበረው የአርበኞች ቁጥር አለመዛመድ ነው፤ ምናልባት ኢጣልያ አሥር ዓመታት ያህል ቢቆይ የኢትዮጵያ ሕዝብ አልበገር ባይነት ይላላ ነበር ብሎ የአርበኞቹን ቁጥር መቀነስና የትጥቅ መፍታቱን መጨመር እንደማስረጃ ሊያቀርበው ፈልጎ ይሆናል።

በአልቤርቶ ስባኪ መረጃ መሠረት የተጎዱ ኢጣልያኖች እአአ ከ1935 እስከ1940 ድረስ 188000 (አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት ሺህ) ይሆናሉ፤ በዚያው ጊዜ ውስጥ የሞቱ 16212 (አሥራ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ አሥራ ሁለት) ነበሩ፤[59] ለኢጣልያ ይህ ቀላል የሚባል ጉዳት አልነበረም፤ የኢጣልያ አገዛዝ በአምስት ዓመታት ውስጥ ተደላድሎ ለመግዛት እንዳልቻለ ያሳያል።

ነገር ግን በአለፉት ሃያ አራት ዓመታት የታየው የኢትዮጵያዊነት ጥንካሬ ኤርትራን ማስገንጠሉን ባያግድም በቀላሉ የሚገመት አይደለም፤ ምናልባት ከአድዋ ጦርነት በኋላ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ወሰን ሲከለል ኤርትራ ከኢትዮጵያ

[59] አለቤርቶ ስባኪ (2)፣ ገ.99.






መውጣትዋን ያስታውስ ይሆናል፤ አሁን ግን በገዛ ልጆችዋ፣ ያውም በትግራይና በኤርትራ ልጆች! በዚህ ላይ ኢጣልያም ባይኖር የኢጣልያ ባንዶች አልነበሩበትም ለማለት አይቻልም፤ ሌላው ማስታወስ ያለብን ኢጣልያ ኤርትራን ከትግራይ ጋር አያይዛ ወደኢትዮጵያ ስታስገባ የባንዳዎቹ ልጆች ትግራይንና ኤርትራን ለይተው፣ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ማስወጣታቸው ነው።

ዋናውን ነገር ልድገመው፡- በኢትዮጵያ ታሪክ እስከዛሬ ከመክሸፍ ያመለጠው የኢትዮጵያ ህልውና ነው፤ በአለፉት መቶ ያህል ዓመታት የኢትዮጵያን ህልውና ክፉኛ የተፈታተነው ጎሠኛነትና ባንዳነት ነው፤ ስለዚህም ስለባንዳነት የምንችለውን ያህል ለማወቅ መጣር ያስፈልገናል፤ አዳፍኔ ባንድነትን ሞሽሮና አከናንቦ እንዳናውቀው አድርጎናል፤ የተረፈውን የኢትዮጵያ ህልውና ለመጠበቅ ባንዳነትንና ጎሠኛነትን ያለይሉኝታ ልንገጥማቸው ይገባል።


## ባንዳነት በኢጣልያ ዘመን

ባንዳ የምንለው ማንን ነው? ባንዳ የምንለው ወገናችን የሆነ ኢትዮጵያዊ ወገኖቹን ሁሉ ከድቶ የጠላት መሣሪያ በመሆን ወገኖቹን በተለያዩ መንገዶች፣ በስለላ፣ በማሳበቅ፣ በአሽከርነት (የባንዳ ሌላው ስሙ አስካሪ ነው፤) በተዋጊነት የሚያገለግል ሎሌ ነው።

የባንዶቹን አስከፊና አሳፋሪ ታሪክ መርሳት በበዙ መንገድ ይጎዳል፤ አንደኛ በሕይወት ያሉት ባንዶች እንዳይጸጸቱና ንስሐ እንዳይገቡ፣ የያዙትንም እውነት እንዳያካፍሉንና ለሚቀጥለው ትውልድ ትምህርት የሚሆን ጸጸት እንዳይተው ማድረግ ነው፤ ሁለተኛ የባንዳዎቹ ልጆች



በትግራይ የነበረው ዋና ባንዳ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ



ትክክለኛውን ታሪክና እውነቱን በማወቅ ከአባቶቻቸው የክህደት ታሪክ ነጻ ወጥተው ከእፍረትና ከመሸማቀቅ ይድናሉ፤ የቤተሰቦቻቸው የባንዳ ታሪክ በልባቸው ውስጥ እንደጦር ተሰክቶባቸው ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን አርበኞች ከነበሩት ጋር እያወዳደሩ ከሚያድርባቸው ጥላቻም ይድናሉ፤ ከሁሉም በላይ ልጆቹ ራሳቸውን በመለወጥ የባንዶች አባቶቻቸውን ታሪክ ለመለወጥ መንገዱ ይከፈትላቸዋል፡፡

የባንዶች አባቶቻቸውን ታሪክ ደብቀው ኑሮአቸውን የሚቀጥሉ ሰዎች የራሳቸውን ታሪክ ከሁለት አማራጮች በአንዱ ውስጥ ያስገባሉ፤ የባንዶች አባቶቻቸውን ታሪክ ደብቀው ሲያፍሩና ሲሸማቀቁ ይኖራሉ፤ ወይም እውነቱን ተቀብለውት በነጻነት ትየኖሩ የራሳቸውን ታሪክ ይኖራሉ፤ የባንዶች ልጆች አንደኛ የልብ ውስጥ እፍረትና የመንፈስ መሸማቀቅ ያድርባቸውና ልበ-ሙሉ ዜጋ መሆን ይሳናቸዋል፤ በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያን ታሪክ ለእነሱና ለአባቶቻቸው እንደሚመች እያደረጉ በመተርጎም የራሳቸውን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያንም ታሪክ ያበላሻሉ፤ እያበላሹም ነው፤ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ታሪክ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች የተለየ ባለመሆኑ ከመቶ ዓመት አይበልጥም የሚባለው





የባንዶች ልጆች የፈጠሩት የሻቢያና የወያኔ ተረት ነው፤ባንዳዎች ያልነበሩ የኤርትራና የትግራይ ሰዎች ይህንን የፈጠራ ታሪክ አይቀበሉትም፤ምክንያቱም የብዙዎቹ አባቶች በኢትዮጵያዊነታቸው ኮርተው በአርበኝነት የሞቱ ወይም የተጎዱ ይሆናሉ፡፡

የባንዶቹ ልጆችና የአርበኞቹ ልጆች ታሪክ አንድ ሊሆን አይችልም፤ ስለዚህም የባንዶቹ ልጆች ሲያይሉ የአባቶቻቸውን የጎደፈ ታሪክ ለመደበቅ የአርበኞችንና የአገር ወዳዶችን ዜጎች ታሪክ ይደመስሱታል፤ የባንዳዎች ልጆች ራሳቸውን ቀና ማድረግ የሚችሉት ሌላውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዲያውም አገሪቱን ጭምር በባንዳ ደረጃ ሲያወርዱ ብቻ ይመስላቸዋል፤ በኢትዮጵያ የአርበኞች ታሪክ ያልተጻፈው ለዚህ ነው፤ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በስልጣን ላይ የወጡት ስደተኞችና ባንዶች የአርበኞችን ታሪክ መጻፍና አጉልቶ ማሳወቅ እነሱን የሚያሸማቅቃቸው ነበርና ምሥጢር አድርገውት አለፉ፤ ከታሪክ ምሁራኑም ውስጥ ይህንን አስፈላጊ ሥራ አጥንቶና ተመራምሮ ሊያሳውቀን የደፈረ የለም፤ ምናልባት ጠገራ ብር አላዩበትም ይሆናል፤ እንዲያውም የየካቲት አሥራ ሁለትን አበሳ የጻፈልን ፈረንጅ ነው፤[60] ኢትዮጵያውያን የታሪክ ባለሙያዎች አላሰቡትም፤ በቅርቡ ደግሞ የአርበኞችን ታሪክ አንድ ፈረንጅ ሳይጽፍልን አይቀርም፤ በአገር ውስጥ አቶ ታዴዎስ ታንቱ ከዚህም ከዚያም የአርበኞችን ታሪክ እየሰበሰበ የአንድ ሰው የብቻ ጥረት የሚፈቅድለትን ያህል በጋዜጣ እያወጣ ነው፡፡

[60] አዶለፍ ፖርስላከ፣ ተርጓሚ ተሜነ ጀብሬ መኮንን፣ የሀበሻ ጀብዱ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ አዲስ አበባ፣ 1989.





የመንፈሳዊ መሪዎች የሚባሉትም ለጠላት ገብረዋል፤ ክርስቲያኑም



...... እስላሙም







*ገበዝ ባንዳ!*

ደጃዝማች ግርማቸው ይህንን ትዝብታቸውን በቅሬታ አስፍረዋል፤ አንዱ ባንዳ፣ ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ በሮማ ብርሃን ጋዜጣ ላይ የሚከተለውን ውዳሴ ፋሺስት ጽፈው ነበር፤--

*ደምጹ ሲያስተጋባ ከሩቅ የሚሰማው*
*የአማኑኤል መድፉ ወልደ ነጎድጓድ ነው።*
*ሁለት ጊዜ ንጉሥ ሦስተኛ ቄሣር*
*ማን አግኝቶ ያውቃል ያንተን ያህል ክብር።*[61]

*ያማኑኤል ብልሃት ያማኑኤል ጥበብ*
*ቢቆጠር አያልቅም እንደሰማይ ኮከብ።*
*ዘውድና ሉል ሁሉ ምንኛ ዘየደ*
*ለታላቁ ንጉሥ አደረ እየሄደ።*

[61] ዘርፈ ታሪኩ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ **ፍቁረ-ፋሺስት ግጥሞች** ፤ የሮማ ብርሃን ኅዳር፣ 1932 ዓ.ም. ገ. 3-4.




የመንፈሳዊ መሪዎች የሚባሉትም ለጠላት ገብረዋል፤ ክርስቲያኑም



...... እስላሙም



ጎበዝ ባንዳ!

ደጃዝማች ግርማቸው ይህንን ትዝብታቸውን
አስፍረዋል፤ አንዱ ባንዳ፤ ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ
በሮማ ብርሃን ጋዜጣ ላይ የሚከተለውን ውዳሴ ፊሺስት
ነበር፤--

*ደምጹ ሲያስተጋባ ከሩቅ የሚሰማው*
*የአማኑኤል መድፉ ወልደ ነጎድጓድ ነው፡፡*
*ሁለት ጊዜ ንጉሥ ሦስተኛ ቄሣር*
*ማን አግኝቶ ያውቃል ያንተን ያህል ክብር፡፡*[61]

*ያማኑኤል ብልሃት ያማኑኤል ጥበብ*
*ቢቆጠር አያልቅም እንደሰማይ ኮከብ፡፡*
*ዘውድና ሉል ሁሉ ምንኛ ዘየደ*
*ለታላቁ ንጉሥ አደረ እየሄደ፡፡*

[61] ዘርፌ ታሪኩ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ ፍቁረ-ፋሺስት ግጥሞች ፡ የሮማ ብርሃን ኅዳር፣ 1932 ዓ.ም. ገ. 3-4.

የኂለው የማስታወቂያ ምክትል ሚኒስትር የፋሺስትን ኃይል ሲገልጹ

*በሰማይ ሲበሩ ነፋስ አይነካቸው፣*
*በመንገድ ሲሄዱ እንቅፋት የላቸው፣*
*በባሕር ቢሄዱ ማዕበል አይነካቸው፤*

*ብለው ሲደመድሙ፡-*

*ከክርስቶስ በታች ከኛ በላይ ናቸው፤*
*እንዲህ አድርጎ ነው አምላክ የሰጣቸው፡፡*[62]

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዙፋናቸው ላይ ከተመለሱ በኋላ ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ የሚከተለውን ዘመሩ፤--

*ወላድ ኢትዮጵያ ውድ አገራችን*
*አስማምታ የምትወልድ ጀግና ጀግናውን፡፡*
*የጭንቅ ምጥ ይዟት ተጨንቃ ሳለች*
*በኃይለ ሥላሴ ተገላገለች፡፡*[63]

በፊት በኢጣልያ ወረራ ዘመን የሚከተለውን ዘፍነው ነበር፡፡

**እግዜር ላነገሠው ለሾመው ቀብቶ**
**መገዛት ይገባል ኀሊናን አቅንቶ፡፡**[64]

አቶ ከበደ ሚካኤል፣ አቶ ዓምደ ሚካኤል ደሳለኝና አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ (በኋላ ብላታ) የፋሺስት ኢጣልያ አገልጋይ ሆነው ከቆዩ በኋላ ተቀልብሰው ዘመዶቻቸውና ወዳጆቻቸው እንደሚሉት ወደውስጥ አርበኛነት ተለወጡ፤ የውስጥ

[62] ዝኒ ከማሁ፤ ገ. 4.
[63] ዝኒ ከማሁ ገ. 6
[64]ዝኒ ከማሁ ገ. 7.





አርበኛነትን ካነሣን አንድ ከእውነተኛ ምንጭ ያገኘሁትን ታሪክ ልናገር፤ በኢጣልያ ወረራ ዘመን አንድ አቶ ዮሐንስ ረምሀ የሚባሉ የትግራይ ሰው ከወይዘሮ ገነት ወልደ ገብርኤል ቤት ተከራይተው ይኖራሉ፤ አቶ ዮሐንስ ቆንጆ ሚስት ያገቡና ቤታቸውን ወደጠጅ ቤት ይለውጡታል፤ ተከራይተው የሚኖሩት በወይዘሮ ገነት ወልደ ገብርኤል ቤት ውስጥ ነው፤ በዚህ ጠጅ ቤት ባንዶች ሁሉ እየገቡ ገበያው ደርቶላቸዋል፤ ግን ለብዙ ወራት ለወይዘሮ ገነት የቤቱን ኪራይ አልከፈሉም፤ ወይዘሮ ገነትም አልጠየቁም፤ አንድ ቀን አቶ ዮሐንስ ወደወይዘሮ ገነት ቤት ሄደው የሚከተለውን ዓይነት ነገር ይነግሯቸዋል፤-- ‹‹ታሪክሽን በደንብ አጥንቼአለሁ፤ እኔ ግን ለአንቺ በሚስቴ እየነገድሁ ገንዘብ የምሰበስብ እመስልሽ ይሆናል፤ ሴትዮዋም ሚስቴ አይደለችም፤ እኔም የምሠራው ለአርበኞች መሣሪያ እየሰበሰብሁ ለማስተላለፍ ነው፤ እስካሁን የቤቱን ኪራይ ያልከፈልሁሽ በዚህ ምክንያት ነው፤ ወደፊትም አልከፍልሽም፤ እወቂው፡፡›› ይሏቸዋል፤ ወይዘሮ ገነትም ሳያስቡት በአቶ ዮሐንስ ረምሐ መልማይነት የውስጥ አርበኛ ይሆናሉ፡፡

<u>ባንዳነት በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን</u>

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከስደት ተመልሰው መንግሥት ሲያቋቁሙ በመጀመሪያ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከሰጡት መመሪያዎች አንዱ በኢትዮጵያ ውስጥ በነበሩ ፋሺስት ኢጣልያኖችና ባንዶች ላይ ምንም የበቀል እርምጃ እንዳይወሰድባቸው መከልከል ነበር፤ ይህን ትልቅ የመንፈስ ገናናነትን የሚያሳይ የምሕረትንና የይቅር ለእግዚአብሔር ባይነትን በበኩሌ እደግፈዋለሁ፤ ነገር ግን የቂም እርምጃን መከልከል ፋሺስት ኢጣልያ ከፋሺስት የኢጣልያ ወታደሮችዋ ጋር ኢትዮጵያን መውረርዋንና በጋዝ ጭስ ጭምር የኢትዮጵያን ሕዝብ መጨፍጨፍዋን አይፍቀውም፤ ለኢጣልያ የገበሩና አሽከርነት ያደሩ ወገኖች ባንዶቿ ሆነው በወገኖቻቸውና በአገራቸው ላይ የፈጸሙቋቸውን አስነዋሪ፣ አሳፋሪና ጎጂ ድርጊቶች ይቅርታ አይሰርዘውም፡፡

በአንድ በኩል አርበኞች አምስት ዓመታት በሙሉ በዱርና በገደል እየተንከራተቱ ሰንደቅ ዓላማቸውን ሳያሳጥፉ ሲዋጉና የመጨረሻውን መስዋእትነት ሲከፍሉ ቆይተዋል፤ የተዋጉለትና የሞቱለት ነጻነት ከተገኘ በኋላ ግን እነሱ ወደኋላ ተገፍተው በስደተኞችና በባንዶች መቀደማቸው አዲስ ሁኔታን ፈጠረ፤ ይህ ሁኔታ አርበኝነት መክሸፉን የሚያመለክት ነው፤ ከዚያም በላይ ባንዳነትና ስደተኛነት የሚያዋጣና የተሻለ ምርጫ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፤ አርበኝነት ከሽፎ ባንዳነትና ስደተኛነት ሲከበር የታሪክ መዘውር ተለወጠ ማለት ነው፤ የሚከተለው ትውልድ ከአርበኝነት ይልቅ ባንዳነትንና ስደተኛነትን ይመርጣል ማለት ነው፤ ዛሬ ይህንን እያየን ካልሆነ መክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ የተሟላ መልእክት አልያዘም ማለት ነው፤ ይህንን ገሀድ ነገር ከዚህ በላይ ለማስረዳት አልሞክርም።

የኢጣልያ ወራሪ ኃይል ከኢትዮጵያ ወጥቶ ከሄደ በኋላ ኢትዮጵያውያን የነበራቸው ኩራትና ክብር በይፋ የሚታይ ነበር፤ ከልጅ እስከደቂቅ አንገቱን ከፍ አድርጎ በየትም ቦታና ጊዜ ኩራቱንና ክብሩን ይጠብቅ ነበር፤ ደሀነት የኢትዮጵያዊነት መንፈስን አያጎድፈውም ወይም አይቀንሰውም ነበር፤ ደሀ ሆኖ ክብሩን ይጠብቅ ክብሩም ይጠበቅለት ነበር።

አገር ከተረጋጋ በኋላ ግን አጼ ኃይለ ሥላሴ በአገዛዛቸው ውስጥ ቀስ እያሉ መጀመሪያ እንደሳቸው በስደት ለነበሩት ቀጥለውም ለባንዳዎች ቅድሚያ እየሰጡ መሾም ጀመሩ፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ ይህንን ያደረጉት በሁለት ምክንያቶች ነው ይባላል፤ አንዱ የሠለጠነ የሰው ኃይል ያለው በባንዳዎቹና በስደተኞቹ መሀከል ስለሆነ፤ እንግዲህ ከጎንደር ዘመን በኋላ የፈረንጅ አሽከር መሆን መጥቀም የጀመረው በዚያን ጊዜ ነው ማለት ነው።

የአጼ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ አርበኞችን ችላ ብሎ ባንዳዎችንና ስደተኞችን በሥልጣን ወንበር ላይ ማስቀመጡ ከላይ እንደተገለጸው በጫካ ውስጥ ከቆዩት አርበኞች ይልቅ ስደተኞቹና ባንዳዎቹ የፈረንጅ አሽከር በመሆን የሠለጠኑ በመሆናቸው ሊሆን ይችላል፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ ሌሎችም ምክንያቶች እንደነበሯቸው መገመት አያስቸግርም፤ መጀመሪያ ነገር እሳቸው ራሳቸው ስደተኛ





ነበሩ፤ በዚህም የተነሣ ተቃውሞ ነበረ፤ አርበኛው በበላይነት ትከሻውን እያሳየ ከሚያሸማቅቃቸው ባንዶችና ስደተኞች ጭራቸውን እየቆሉ ፍጹም ታማኝ ሎሌዎች ሆነው እንደሚያገለግሏቸው ያውቃሉ፤ አንዱ የባንዳዎችና የስደተኞች አገልግሎት የአርበኞችን ኩራት (ባላጋራዎቻቸው ትዕቢት የሚሉት ይመስለኛል፤) የሚመክትላቸውና ሥልጣናቸውን የሚያረጋግጥላቸው መሆኑ ነው።

ለማናቸውም ባንዶችና ስደተኞች ሥልጡኖች ተብለው እልፍኝ ገቡ፤ በአርበኞችና ስደተኞች በአንድ በኩል፣ በጃንሆይና በባንዶች በሌላ በኩል የነበረውን ግብግብ ትንሽም ቢሆን ቢትወደድ ዘውዴ ገልጸውታል፤ ከንቲባ ታከለ በማዘጋጃ ቤቱ ውስጥ ኢጣልያኖች ትተውት የሄዱትን ‹‹የኢትዮጵያውያንን ወይዛዝርትና መኳንንት የሕይወት ታሪክና ለኢጣልያ መንግሥትም ያቀረቡትን አገልግሎትና የተከፈላቸውንም ውለታ የሚያሳይ››[65] ሰነድ እየሰበሰቡ በማደራጀት ላይ እንደነበሩ ቢትወደድ ዘውዴ ያውቁ ነበር፤ በኋላ በባንዶቹ ሰነዶች ውስጥ ስማቸው ከነበረው መሀል ጥቂቶቹ በጃንሆይ በይፋ ሲሾሙ ከንቲባ ታከለ ወልደ ሐዋርያት የባንዶቹን ሰነድ ይዘው ጃንሆይ ዘንድ ቀርበው፤-

*‹ብእነዚህ ሰዎች እኔ አንሼ ነው ለሚኒስትርነት ያልተመረጥሁት? እነዚህ እኮ ለፋሺስት ኢጣልያ ያገለገሉ ናቸው፤ እያንዳንዱ ምን ዓይነት አገልግሎት እንዳቀረበ፣ አልፎ አልፎም ስለዚያ ውለታው ከኢጣልያ ምን እንደተከፈለው፣ ምን ዓይነት የማዕርግ ስም እንዳገኘ የሚያሳይ መዝገብ ተገኝቶ እኔና ዘውዴ እያሰናዳን ነው የምንገኘው›*[66]

ከጥቂት ቀናት በኋላ ጃንሆይ ከንቲባ ዘውዴን ጠርተው የባንዳዎቹን ሰነድ **‹‹ብል አሁን ሂደህ ለአባ ሐና ጂማና ለፊታውራሪ እስፋው ከበደ አስረክብ፤››** ተብለው ታዘዙ፤ **‹‹በዚያው ሌሊት ከእነርሱ ጋር ወደአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሄደን**

[65] ዘውዴ ገብረ ሕይወት፣ የሕይወት ውጣ ውረድ፣ 1995፣ አዲስ አበባ፣ ገ. 108.
[66] ዝኒ ከማሁ፣ ገ. 109.

*መዛግብቱን በሙሉ አስረክቤ በዚያው ሌሊት በካሚዮን ተጭነው ቤተ መንግሥት ተወሰዱ።››*[67]

አንድ ፈረንጅ ስለማይጨው ዘመቻ በጻፈው ውስጥ አንድ አብቹ ስለሚባል የሰላሌ ጀግና ወጣት አንብቤ ከልቤ አልወጣ ብሎኛል፤ መረጃ ለማግኘት ሱሉልታ ተመላልሼ አልሆነልኝም፤ ጉልበት ካለቀ በኋላ ሆነና ... ከደጃዝማች አበራ ካሣ ጋር ማይጨው ዘምቶ የነበረው የሰላሌ ወጣት ‹‹ይቺ ልጅ›› በመባል ይታወቅ ነበር፤ አብቹ፤ ሊረሳ አይገባም፤ አንድ ሰው ታሪኩን ቆፍሮ ማውጣት አለበት።

[67] ዝኒ ከማሁ፣ ገ. ፻፲.





# *ምዕራፍ ፰*
# *በመክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የቀረቡ ትችቶች*

ትችት አንድ የማዕርጉ በዛብህ ትችት[68]

የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም አዲሱ "መክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ" የተባለው መጽሐፍ በኢትዮጵያ የስነ ጽሁፍ ታሪክ ፈረንጆች እንደሚሉት እንደ አንድ የቦምብ ፍንዳታ የሚታይ ኩነት ነው። የመጽሐፉ ርዕስ አስደንጋጭ ከመሆኑም በላይ አዕምሮን የሚኮረኩር ነው። ከዚያም አልፎ ርዕሱ ኢትዮጵያ ውለታ የከፈለችው ለአገራቸው ህልውናና ነፃነት ለተዋደቁት ጀግኖች አርበኞቿ ሳይሆን ለባንዶች ነው በሚለው ግጥም ታጅቧል። በመጽሐፉ የፊት ሽፋን በኢጣሊያ ፋሽስት አውሬዎች አንገቱ ተቆርጦ ለመቀጣጫ የቀረበውና በመጽሐፉ ርዕስ የውስጥ ማስተዋወቂያ ገጽ እንዲሁም በመጽሐፉ መጨረሻ ገጾች የቀረቡት ፎቶግራፎች ሁሉ ሁለት አሳዛኝ ዕውነቶችን የሚገልፁ ናቸው። አንደኛው ዕውነት የሰለጠኑና ክርስቲያኖች ናቸው የተባሉት የኢጣልያ ፋሽስቶች በዱር ከሚገኝ አውሬ ባላነሰ ጭካኔና በደመነብስ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈፀሙት ኢሰብአዊ ወንጀል ይቅር ይባል እንደሆን እንጂ ፈጽሞ ሊረሳ የማይገባ መሆኑን በጽናት የሚገልፅ ነው። ሁለተኛው ፕሮፌሰር መስፍን ሊያሳስበን የሚፈልገው ዕውነት ደግሞ አገራችን በነፃነት፣ ባለፉት ተከታታይ ሰባ ዓመቶች የኖሩት ኢትዮጵያውያን እኛንም ጨምሮ በሕይወት

[68] ማዕርጉ በዛብህ በሰንደቅ ጋዜጣ ላይ

እየኖርን ያለነው እነኛ ፎቶግራፎቻቸው በዚህ መጽሐፍ የሚታየው አያሌ ሺዎች ኢትዮጵያውያን ሰማዕታት በከፈሉት መስዋዕትነት መሆኑን በጽናት እንድናስበው ነው። ይህንን ከባድ ታሪካዊ ዕዳ የምንከፍልበት ዘዴ እንኳን ብናጣ ባለዕዳነታችን በጽናት እየተሰማን ውለታውን እያስታወስን መኖር ይገባናል ለማለት ነው- ፕሮፌሰሩ፤

*ሞታችሁ ለኛ ሕይወት*
*ሰቃያችሁ ለኛ ልማት*
*ውርደታችሁ ለኛ ክብር...*
*ዕዳችሁን ለመክፈል ባልችልም*
*እንዳለብኝ አምናለሁ።...*

ሲል በግጥም የገለፀው።

ፕሮፌሰር መስፍን (የማከብረው አስተማሪዬ) ስለሆነ አንተ እያልኩ ነው የምጠቅሰው። እስከዛሬ ከፃፉቸው መፃሕፍት ይኸኛው መጽሐፍ ስለግፍ ያለውን ታላቅ ተቆርቋሪነት፣ ቁጭቱን፣ ያልተገደበ ምሁራዊ ምስክርነቱን የገለፀበት መጽሐፍ ነው ማለት ይቻላል። ስለሆነም ጉዳዮቹን መረርና ከረር ባለ ቋንቋና ዘይቤ በማቅረቡ ጨለምተኛ ድርሰትም ሊመስል ይችላል። እርሱም ይህንን በመገንዘብ ነው "... መጽሐፉ በጠቅላላ፣ በተለይ ይህ መቅድም የከረረ ንዴት መግለጫ ነው፤" የሚለው።

ፕሮፌሰር መስፍን በዚህ መጽሐፍ የሚተርካቸውና የሚተነትናቸው አንኳር ጉዳዮች ብዙ ናቸው። ኢትዮጵያ ወዴትና እንዴት ነበረች? ዛሬ የት ነች? ወዴትስ እየሄደች ነው የሚሉትን ከባድ ጥያቄዎች ከማንሳትና ከመመለስ አኳያ ደራሲው ከፍርሃትና ከይሉኝታ ነፃ በሆነ ምሁራዊ ምርምር ያቀረባቸው ቁምነገሮች መጽሐፉን ልዩ ያደርጉታል። አንባቢ ማውጫውን ገለጥ አድርጎ ሲያይ "መክሸፍ በኢትዮጵያ ታሪክ" ታሪክ ምንድን ነው፣ የታሪክ አስተሳሰብ፣ የኢትዮጵያ ታሪክና ቂሳራውያን ምሁራን፣ የኢትዮጵያ ታሪክና ዘመናውያን የኢትዮጵያ ታሪክ ሲቃውንት፣ አጼ ዮሐንስና የህይወት ውል፣ አጼ ምኒልክና የውጫሌ ውል፣ የቄሣራውያን





ኃይሎች ግፊትና የአድዋ ጦርነት፣ መንደርተኝነትና ሕዝብነት፣ አድዋ፣ ማይጨው፣ ጅጅጋ ወዘተ የሚሉ ጎንዑሳን ርዕሶችን ያገኛል - ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል። እነኝህ ርዕሶች ደግሞ የአገሩ ጉዳይ ለሚያሳስበውና ለሚከነክነው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለንባብ የሚያጓጉና የሚያከራክሩ ጉዳዮች ስለሆኑ መጽሐፉን ከፍተኛ ዋጋ ይሰጡታል። የአንባቢን ቀልብ በጽናት ይስባሉ። ለዚህም ነው መጽሐፉ ብዙ ትችቶች እያስተናገደ ያለው።

መጽሐፉ በአሁኑ ወቅት ለምን ተፃፈ? ለምንስ የመጽሐፉ ርዕስ የከረረና ጨለምተኛ መልዕክት የሚያስተላልፍ መሰለ? ለሚሉ ጥያቄዎች ፕሮፌሰር እንደተለመደው ብዙ አሳማኝ ክርክሮችን በማንሳት የመንግሥት መገናኛ ብዙሀን የሚስሉልንን ሳይሆን ዕውነተኛውን ኢትዮጵያን በገሃድ እንድናያትና ያሳለፈቻቸውንና ዛሬም የተደቀኑባትን ችግሮችና ሰቆቃዎች እንደዜጎች ይበልጥ ተገንዝበን ሌላው ቢቀር ላገራችን ሀቀኛ ህልውናና እድገት ይበልጥ እንድናስብ ሊያደርገን የሚችል ይመስለኛል። በአጠቃላይ የፕሮፌሰር መስፍን ጽሁፎች በተለይም ይህ መጽሐፍ፤ ብዙዎቻችን የማናያቸውን የአገራችንን ልዩ ታሪክና አገራዊ ባህሪያት፣ የሕዝቦቻችንን ትልቅነት እንዲሁም ያሉብንን ጉድለቶችና ችግሮች፣ ወደፊትም ሊገጥሙን የሚችሉትን ተግዳሮቶች ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩ ናቸው።

በተለይ ይህ መጽሐፍ የብዙዎችን አንባቢዎች ቀልብ የሚስበው በሁለት ምክንያቶች ይመስለኛል። አንደኛ በመጽሐፉ ስም ወይም ርዕስ ላይ የተቀመጠው "መክሸፍ" የሚለው አሉታዊና አስደንጋጭ ቃል ሲሆን፤ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ፀሐፊው ሌላ ሰው ሳይሆን ደፋሩ ደራሲ መስፍን ወልደማርያም መሆኑ ነው። ታዲያ ፕሮፌሰር "መክሸፍ" የሚለውን ቃል ሲፈታውና ሲያብራራው፤

*"መክሸፍ የምለው አንድ የተጀመረ ነገር ሳይጠናቀቅ ወይም ሳይሳካ እንቅፋት ገጥሞት መቀጠል ሳይችል፣ ዓላማው ሲደናቀፍና በፊት ከነበረበት ምንም ያህል ወደፊት ሳይራመድ መቅረቱን ነው፤ የእድገት፣ የመሻሻል፣ የመለወጥ ጉዞ*

*መቋረጥን የሚያመለክት ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ታሪክ አብዛኛውን ጊዜ ከታችኛው ደረጃ ወደላይኛው ደረጃ የሚያደርስ፣ ከተጎሳቆለ ኑሮ ወደተሻለ ኑሮ የሚያመጣውን ጉዞ የሚያመለክት የእድገት ጎዳና ሆኖ ይታያል" ካለ በኋላ በተጨባጭ ምሳሌ የቃሉን ትርጉም ይበልጥ ሲያብራራው ደግሞ ካልተለወጡ ወደባሰ ደረጃ መውረዱ የማይቀር ነው፤ ወይም በሌላ አነጋገር ካላደጉና ካልተሻሻሉ መሻገትና መበስበስ፣ በስብሶ መፈራረስ ግዴታ ነው" ይላል:: አስፈሪ ዕውነት ነው::*

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተነሱ አሳዛኝና አስቆጪ ቁምነገሮች ብዙ ናቸው:: አንዳንዶችን ለመጥቀስ ያህል ፕሮፌሰር መስፍን ብዙ ጊዜ በቁጭት ከሚገልፃቸው የኢትዮጵያ ታሪካዊ ችግሮች አንዱ አገሪትዋ ለዘመናት ያሳለፈቻቸውና የምትገኝበት የፖለቲካ ጭቆና ጉዳይ ነው:: ይህ ዕውነት ሁላችንንም ቢያሳዝነንም እንደ ፕሮፌሰር መስፍን በቁጭት ደጋግመን የገለጽንበት ጊዜ የለም:: በኢትዮጵያ በየጊዜው የመጡ መሪዎች የየራሳቸውን ጥቅምና ክብር በማስጠበቅና በማስቀደም፣ የሕዝቡን ስልጣን ነጥቀው፣ ሕዝቡ ስለመብቱ እንዳያስብና ብሎም ሃሳቡን በነፃነት እንዳይገልጽ ስላደረጉት አገሪትዋ ወደተሻለ እድገት ልትሸጋገር አልቻለችም:: አንዳንድ ጊዜም ከ"ባለህበት ጽና" ወደ "ቀኝ ኋላ ዙር" ያመራችበት ጊዜ አለ:: በመሆኑም አልፎ አልፎ የሚታየው መልካም ውጤት ተመልሶ ሲከሽፍ ይታያል ይላል ፕሮፌሰር መስፍን:: መክሸፍ የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ በምሳሌ ለማስረዳት ፕሮፌሰር መስፍን አያሌ ጉዳዮች ከመጥቀሱም በላይ በዋናነት የአድዋንና የማይጨው ጦርነቶችን ታሪክ ያወሳል:: አያቶቻችንና ቅድመ አያቶቻችን በሰለጠኑ ሠራዊትና በላቀ ትጥቅና ስንቅ የደረጀውን ወራሪውን የጣሊያን ጦር ድባቅ በመምታት ለአገራቸው ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው የጥቁር ዘር ታሪካዊ ድል አስገኙ:: ከዚያ በኋላ ግን ለሚቀጥሉት 40 ዓመታት ኢትዮጵያ ምንም ዓይነት እድገት ሳታሳይ ተቀምጣ ጠበቀች:: ፋሺስት ኢጣልያም ይህንን ዕድል ተጠቅሞ የአድዋን ድል ሽንፈት ከታሪክ መዛግብት መሰረዝ የሚቻል መስሏት ይበልጥ ተዘጋጅታና





ተደራጅታ፣ ማይጨው ላይ ንጉሱንና ጦራቸውን በማሸነፍ አንፀባራቂውን የአድዋን ድላችንን ለማክሸፍ ሞክራለች:: ያ ታላቁ የአድዋ ድላችን ግን የታሪክ ዕንቁ ስለሆነ ሊጠፋ ባይችልም የማይጨው ሽንፈታችንን ፕሮፌሰር መስፍን እንደታሪክ መክሸፍ ምሳሌ ያቀርበዋል:: የፕሮፌሰሩ ቁጭት አርባ ዓመት ሙሉ እንዴት ሳንንቀሳቀስ፣ ሳናድግ፣ ጣሊያኖችን ሳንዘጋጅ ያን ጊዜ ጥለውን እንደሄዱት ቁጭ ብለን ጠበቅናቸው ነው:: ይህ ጉዳይ በአገራችን ምሁራን ተነስቶ የማያውቅ አቢይ ነጥብ ነው:: አከታትሎም ፕሮፌሰር እንደ ሕዝባዊ ባህርያት ወይም ልማዶች ሆነው ሲጐዱን የኖሩትን አሳፋሪ ጠባዮች እንደሚከተለው ያስቀምጣቸዋል::

*"ትምህርት ለኑሮን ወይም ትምህርት ለህይወትን ንቀን፣ ትምህርት ለሞትን መረጥን፤ በራስ መተማመንን ትተን ጥገኝነትን ወይም ሎሌነትን መረጥን፤ መተባበርን ጠልተን ሁሌም በበትር እንገዛለን፤ ሃሳባችንን እንዳንገልጽ ተለጉመን የሚጐዱንን ትዕዛዞች ሁሉ ለመፈፀም እየተሻማን መጋደልን እንመርጣለን፤ በፍቅር የሚጠጋንን እንርቃለን፣ በዱላ ወደሚያስፈራሩን ለመጠጋትና ዱላውንም ለመሸከም እንሽቀዳደማለን፤ የኀሊናችንን ድምፅ አፍነን የሬዲዮኑን ድምጽ እናስተጋባለን፤ የኑሮ መመሪያችን ከሆድ በላይ ነፋስ ነው፤" ይላል ፕሮፌሰር መስፍን የአገራዊ ድክመቶቻችንን ምክንያቶች ሲነግረን:: ማን ይህንን አንስቶ ያውቃል ከዚህ በፊት?*

ታሪክ የነገሥታትና የመሣፍንት፤ የራሶች፣ የቢትወደዶች፣ ከዚያም ወረድ ብሎ የደጃዝማቾችና የፊታውራሪዎች ገድል ብቻ ሆኖ ሲነገርና ሲፃፍ በኖረበት አገር፤ ታሪክ ለሚለው አከራካሪ ጽንሰ ሃሳብ አዲስ ትርጉም ይዞ ብቅ ማለቱ ፕሮፌሰር መስፍንን በታሪክ ምሁራን ሸንጎ የሚያስቀምጠው እንደሚሆን ማሰብ ይቻላል:: "ታሪክ" ይላል ጋሽ መስፍን "የሕዝብ ተከታታይ ትውልዶች ሥራ ነው፣ ትግል ነው፣ ተጋድሎ ነው፤ እያንዳንዱ የቀደመው ትውልድ ኀብረቱን፣ ንብረቱንና መብቱን በአጠቃላይ

የአብሮ መኖር ሕልውናውን አረጋግጦ ለሚቀጥለው ትውልድ ያስተላለፈውንና ያስተላለፈበትን ሁኔታ ጭምር የሚገልጽ ቅርስ ነው" ይላል፡፡ ይህ ደግሞ የማርክሳውያንን የታሪክ ምሁራን ይመስለኛል፤ ጋሽ መስፍንን በዚያ ባልጠረጥረውም፡፡ ስለቃሉ ትርጉም የታሪክ ምሁራን ሊሟገቱበት የሚችሉ ቢሆንም፤ በዚህ ጸሐፊ አስተያየት "ታሪክ የሕዝብ ተከታታይ ትውልዶች ሥራ ነው" የሚለው አባባል ዕውነት ከመሆኑም በላይ በሕዝብ አዕምሮ አዲስ አብዮታዊ ዕውቀትና አስተሳሰብ የሚያስርጽ ስለሆነ የሚደነቅና የሚጠቅም ምሁራዊ አበርክቶ ነው፡፡

ሌላው ከታሪክ ጋር በማያያዝ ፕሮፌሰር መስፍን ያነሳቸው አበይት ቁምነገሮች ስለታሪክ አፃፃፍና ስለታሪክ ትምህርት የሰጣቸው ሁለት አስተያየቶች ናቸው፡፡ በፕሮፌሰር አስተያየት የታሪክ ምሁራን ታሪክን ከተረት በመለየት አጣርተው "በቋንቋም ሆነ በማናቸውም ባህል" በባዕድ ተጽዕኖ ሳይወድቁ በአገራችን ጥንታዊ መረጃዎች ላይ በመመስረት መፃፍ አለባቸው ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ስለኢትዮጵያ ታሪክ ለመፃፍ የእኛ ምሁራን ፈረንጆች "ለራሳቸው ዓላማ የወረወሩትን ሁሉ እየለቀሙ ያልተማሩትን ፈረንጆች በማስተማር ላይ" ያተኮረ ድርሳን መፃፍ የለባቸውም ይላል፡፡

ሁለተኛው አስተያየት ደግሞ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች የአገራቸውን ታሪክ በፈረንጅ አስተማሪዎች ሊማሩ አይገባም የሚል ነው፡፡ ከዚያም አልፎ "የኢትዮጵያን ታሪክ ለኢትዮጵያ ወጣቶች የሚያስተምረው ፈረንጅ ሁሉ የራሱን አገር ታሪክ ለራሱ አገር ልጆች አስተምሮ የማያውቅ ነው" ይላል ፕሮፌሰር መስፍን፡፡ "ታሪክን የሚያጣምመው የጊዜ ርቀት ብቻ አይደለም፤ አንዳንዴም የቦታ ርቀት ባዕድ ልምዶችና መመዘኛዎች ታሪክን ያጣምማሉ" የሚለው ፕሮፌሰር መስፍን የጠቀሰው የአላን ኔቪን አስተያየት እኔም የምጋራው ሲሆን፤ ጋሽ መስፍን ከፍ ብሎ ያቀረባቸውን ሙግቶች የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡

የ"መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ" ደራሲ ስለታሪክ እና ኢትዮጵያውያን ስለታሪክ ሊኖራቸው የሚገባውን ግንዛቤ ሲያጠቃልል





"... የኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ ኢትዮጵያውያን የታሪክ ባለሙያዎች የታሪክ ስሜት እንዲኖረን ያሻል፤ እኔ የታሪክ ስሜት የምለው እያንዳንዱ በዛሬው ዘመን ውስጥ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ተገንጥሎ ለብቻው የሚኖር ሳይሆን፤ ቀድመው የነበሩ የብዙ ትውልዶች የልፋት፣ የጥረትና የመስዋዕትነት ውጤት በመሆኑ ከበስተጀርባው የነዚህን ትውልዶች ቅርስ ሁሉ ተሸክሞ የቆመ መሆኑን እንዲያውቅ ያስፈልጋል፤ የዛሬውም ትውልድ በበኩሉ የራሱን ቅርስ ጨምሮበት ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ የመንፈስ ግዴታ እንዳለበት ማወቅ ይገባዋል" ይላል፡፡

ፕሮፌሰር መስፍን በምሁራን እስከዛሬ ብዙ ያልተጠየቁና ያልተመለሱ አበይት ጥያቄዎችን ያነሳል፡፡ ለምሳሌ የአክሱምን ሐውልቶችና የላሊበላን ሕብያተ ክርስቲያናት ማን ሰራቸው ማንስ አሰራቸው? ይላል፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ለረጅም ዘመናት የራሳችን ፊደል ያለን ሕዝብ ስንሆን ለምንድን ነው የራሳችንን ስነጽሑፍ ለማዳበር ያልቻልነው? የቴዎድሮስ መድፍ ለምን አንድ ጊዜ ብቻ ተተኩሶ አቆመ፡፡ ለምንስ የቴዎድሮስ "የኢንዱስትሪ አብዮት" በተከታታይ ዘመናት አልቀጠለም? እጅግ ከባድ መስዋዕትነት የተከፈለበትና ኢትዮጵያን በነፃነት እንድትኖር ያደረጋት አስደናቂው የኢትዮጵያ አርበኝነት አንድ ወጥ ታሪክ ለምን እስከዛሬ አልተፃፈም የሚሉትንና ሌሎቹንም ያነሳና የታሪክ ምሁሮቻችን እነኝህን ጥያቄዎች በትክክል የሚመልሱ ስራዎች እስካልሰጡን ድረስ የታሪክ ትርጉሙና ጥቅሙ ምንድን ነው? ሲል እስከዛሬ በሌሎች የአገራችን ምሁራን ያልተነሱትን አበይት ቁምነገሮች በማንሳቱ ወደድንም ጠላንም ፕሮፌሰር መስፍንን የተለየ ምሁር ያደርገዋል፡፡

አንዱ በመጽሐፉ ውስጥ የተነሳው አቢይ ጉዳይ ደግሞ በአገርና በመንደር ወይም በትውልድ አገር* (መንደርና) በጠቅላላ በአገር አስተሳሰብ መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡ ይህንን ልዩነት ለማስረዳት ያቀረበው ሃሳብ የሰው ልጆች ከመንደርተኛነት ወደ

አገር ዜጋነት ከአገር ዜጋነት ወደ አህጉር ዜጋነት፣ ከአህጉር ዜጋነት ደግሞ ወደ ዓለም አቀፋዊ ዜጋነት ማደግ እንዳለብን አበክሮ የሚያስተምርና የሚመክር ነው:: ሃሳቡን ከርሱ በተሻለ ማስረዳት ስለማይቻል እሱ ያለውን እንዳለ ማቅረቡ ይበልጥ ተመራጭ ነው::

*አገር ማለት በአንድ ዓይነት ሕግና በአንድ መንግሥት ጥላ ሥር የሚተዳደሩ ሰዎች (ሕዝብ) ባለመብት የሆኑበትና የኑሮአቸው መሠረት የሚያደርጉት በወሰን የተከለለና የማይደፈር መሬታቸውን ጨምሮ የሚገልጽ ኀብረት ነው" ይልና፤*

ይበልጥ ሲያብራራው ደግሞ በዘልማድ እርስ በርሳችን ማለት ኢትዮጵያውያን ያንተ አገር እዚያ ነው የኔ እዚህ ነው እያልን ስለ ትውልድ ቀዬዎቻችን (ስለመንደሮቻችን) ከምናወራውም የተለየ ነው ሲል ያስረዳል:: ብዙዎቻችን እነኝህን ልዩነቶች አለማወቃችን የሚያሳፍር ነው:: በመጨመርም፤

*"... አገር የሚባለው መሬት ሕዝብና መንግሥት በሚገባ፣ በውልና በሥርዓት ሲተባበሩ ነው፤ ሦስቱ መሠረታዊ ቃላት መሬት፣ ሕዝብ፣ መንግሥት ናቸው፤ መሬት ብቻውን አገር አይሆንም፣ ሕዝብ ብቻውን አገር አይሆንም፤ መንግሥትም ብቻውን አገር አይሆንም፤ ከሦስቱ ሁለቱንም እንኳን እንደፈለግን ብናጣምር አገር አይወጣቸውም::" ሲል በሰፊው በማብራራት የምናውቀው ነገር ቢሆንም ይበልጥ እንድናስብበት የሚያደርገን ይመስለኛል::*

ዛሬ ዓለም ወደ ዓለም አቀፋዊ አንድነት ወይም ግሎባላይዜሽን በምትገሰግስበት ዘመን ከአገራዊ አስተሳሰብ ይልቅ ቋንቋዊና አካባቢያዊ ብሔርተኝነትን ሙጥኝ ማለት ከተፈጥሮአዊ ዕድገት ጉዳና መውጣት መሆኑ ለአንዳንዶቻችን ስለማይታየን ነው ፕሮፌሰር መስፍን "መንደርተኝነትና ሕዝብነት" ሲል በሰፊው





የሄፈበት:: ለመንደርተኝነት ምሳሌ አፓርታይድ ደቡብ አፍሪካ እንደነበረች በማስታወስ የዚያ መንግሥት መመሪያ የነበረው ፖሊሲ በዘር ላይ የተመሠረተ ኋላ ቀር አስተሳሰብ ሲሆን፤ የተሳሳተው የነጮቹ ፍልስፍናም "ጥቁሮችና ነጮች የተለያዩ ስለሆኑ አብረው በአንድ ሥርዓት ስር በእኩልነት ለመተዳደር" አይችሉም:: ስለሆነም ለየብቻቸው "መንግሥት ማቋቋም አለባቸው" ነው:: የአፓርታይዷ ደቡብ አፍሪካ አስተያየትና አመራር የነበረው:: ይህ ደግሞ በቀድሞዋ ደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ ይባል እንጂ ከአንድነት ይልቅ መገንጠልን ሙጥኝ ብለው በዓለም የሚንቀሳቀሱ ወገኖች ሁሉ የጋራ ባህሪ መሆኑን ነው ፕሮፌሰር ሊያሳየን የሚሞክረው::

"ሕዝብነት በዘር፣ በቋንቋ በኃይማኖት ሳይሆን በረጅም ዘመን ታሪክና ባህል፣ በረጅም ዘመን የአብሮነት የፖለቲካ ታሪክ፣ የአስተዳደር ታሪክ፣ የዳር ድምበር ታሪክ በመቆራኘት አንድ ሕዝብ ሆኖ መኖር ነው" የሚለው ትርጉሙ ዛሬ የአገራችንን ኢትዮጵያንና የብዙዎችን የዓለም አገሮች ዕውነታ የሚገልጽ ትክክለኛ አስተያየት ነው በዚህ ጸሐፊ ዕምነት::

"መክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ" በሚለው የፕሮፌሰር መስፍን መጽሐፍ ከቀረቡት አብዛኛዎቹ ሃሳቦች ጋር የምስማማና እንደውም በአድናቆት የምቀበላቸው ብሆንም፤ የታሪክ ምሁሮቻችን የሚጽፉት በፈረንጆች ጽሁፍ በመመርኮዝና በመስራት ነው በማለት የቀረበውን ትችት ግን ለመቀበል ያስቸግራል:: ራሱ ጋሽ መስፍን በዚሁ መጽሐፍ እንደጠቆመው አገራችን ለረጅም ዘመን የራስዋ ፊደል ያላት ብትሆንም የስነጽሁፍም ሆነ የትረካ ጽሁፍ ልምድ ያልዳበረባት አገር በመሆንዋ ለምሁራኑ የታሪክ ጽሁፍ ምንጭ የሚሆኑ በቂ አገር በቀል ጥንታዊ የጽሁፍ መረጃ ምንጮች መኖራቸው አጠራጣሪ ነው:: ይህ በሌለበት ሁኔታ ስለኢትዮጵያ በውጭ ምሁራን የተፃፉትን መረጃዎች መሠረት አድርጎ መፃፉ ትክክል አይደለም ማለቱን መቀበሉ አስቸጋሪ ይሆናል:: ዕውቀት ዓለም አቀፋዊ ነው:: መላው የዓለም ምሁራን የሚጽፉት፣ የሚመራመሩት፣ ይበልጥ እያጠኑ ሙያዎቻቸውን የሚያዳብሩት ከዚሁ የጋራ ንብረት በሆነው ዓለም አቀፋዊው

የዕውቀት ክምችት ላይ በመመስረት ነው። በየክፍለ ትምህርቱ የተለያየ ባህሪ ምክንያት የምርምርና የጥናት ጥበቦቹ በመጠኑ ይለያዩ ይሆናል እንጂ በአጠቃላይ ካለና ከተከማቸ ዕውቀት ወይም መረጃ መዋዋሱ በዚያ ተመስርቶም የበለጠና ያደገ ሥራ መስራቱ ዓይነተኛ የአካዳሚካዊ ሥራ ባህሪ ይመስለኛል።

*የዚህ አስተያየት ጽሁፍ ዋና ዓላማ የመጽሐፉን የስነጽሁፍ ጥራትና ደረጃ ወይም የርዕዮተ ዓለምም ሆነ ፖለቲካዊ ይዘቱን ለመገምገምና ብይን ለመስጠት አይደለም። መጽሐፉ የያዛቸው እጅግ ከፍተኛ ቁም ነገሮች ደራሲውን የሚደነቁና የሚያስመሰግኑ ስለሆኑ አንዳንዶቹን ነጥቦች በማንሳትና በራሱ በደራሲው ቋንቋ በማብራራት ያላነበቡት ወገኖች በተለይ ወጣቶች እንዲያነቡት ለማበረታታት ነው። ማበረታታቱ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ደግሞ በዚህ አስተያየት አቅራቢ እይታ ችግሮቻችንን ያለይሉኝታና ያለፍርሃት በመግለጽ ፕሮፌሰር መስፍን ግምባር ቀደም የሆነ ምሁር ስለሆነ ከመጽሐፉ አያሌ አዳዲስ መረጃዎችና ትምህርቶች ስለሚገኙ ነው።*

ፕሮፌሰር መስፍን ከአምስትና ከስድስት አስርት ዓመታት ላላነሰ ጊዜ የኢትዮጵያና የሕዝቦችዋ ጉዳይ ዋና ጉዳዩ ነው፣ ያገባኛል ብሎ በጋዜጣ፣ በመጽሔት፣ በመፃሕፍት ሲጽፍ፤ በውይይት ፕሮግራሞች ሲሟገት፣ በሬድዮና በቴሌቪዥን ሲከራከርና ሲያስተምር የኖረ ምሁር ነው። ያለፍርሃት፣ ያለይሉኝታ ለአገሪትዋና ለሕዝቦቿ ጥቅም፣ ለነፃነትና ለፍትሐዊ አስተዳደር ጥብቅና በመቆም ብቻውን ከሦስቱ ተከታታይ መንግሥታት ላይ ተቃውሞ ሲያቀርብና ሲታገል በመኖሩ ከዘመኑ የአገራችን ምሁራን የተለየ ያደርገዋል። ስለአገራችን አሳሳቢ ጉዳዮች ፕሮፌሰር መስፍንን ያህል የፃፈ፣ የተናገረ፣ የተቸ ምሁር ያለ አይመስለኝም። ይህንን አቋሙን የምናደንቅና የምንወድለት እንዳለን ሁሉ "ለምን አርፎ አይቀመጥም" የሚሉና ትግሉን የማይወዱለት እንዳሉም አጋጥሞኛል። ሁለቱን የተለያዩ አቋሞች መያዝ ለእኔም ለነርሱም መብታችን ነው፣ በዘመኑ አነጋገር። ሌላው ፕሮፌሰር መስፍንን ከሌሎቹ የትምህርትና የዕድሜ ጓደኞቹ ምሁራን ልዩ የሚያደርገው "ያስተማረኝን ሕዝብ ውለታ መክፈል





አለብኝ" በሚል ትልቅና ትክክለኛ ውሳኔ በመነሳት ትግሉ የሚያስከትለውንም መስዋዕትነት ሳይሸሽ ያለምንም ፍርሃት ለመቀበል ዝግጁ መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ የታየ ዕውነት ነው።

************************************************

ትችት ሁለት ከሽፈት እና እውነት እኩያ እና መንትያ ሲኾኑ . . .

*by Masresha Mammo* (እሱ እንደጻፈው ነው፤)
Friday, February 1, 2013

"ቁም!" ይህን አስፈሪ የኾነ ትዕዛዝ ስንቶቻችሁ በሕይወታችሁ እንደተገናኛችሁት አላውቅም። በደርግ የአገዛዝ ዘመናት ግን እጅጉን የታወቀ ነበር። አንድ ወታደራዊ ፖሊስ ወይም 'የአብዮት ጠባቂ' በመንገዱ ያገኘውን ሰው በድንገት አስቁሞ የሚያርበደብድበት የትዕዛዝ ቃል ነበር። 'ሕግ' የተላለፈ፣ በተቀመጠለት 'ሥርዐት' በአግባቡ አልሄደም ተብሎ የታሰበ፣ 'ከተፈቀደለት መስመር' የወጣ ሁሉ "ቁም!" ይባል ነበር ያኔ። ከስንት ዘመን በኋላ ዛሬ ፕሮፌሰር መስፍን በመጽሐፋቸው መግቢያ ላይ "ቁም! የሚል ማስጠንቀቂያ ይሰጣሉ። የነደደ/የከረረ ምሬት መገለጫ የኾነውን መጽሐፋቸውን ማንበብ የሚገባው ሰው ምን ዐይነት መኾኑን ለመናገር ሲፈልጉ።

"መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ" የሚለው መጽሐፋቸው በእውነትም አሁን ባለችው ኢትዮጵያ አጠቃላይ ኹኔታ ለማይናደድ፣ ለማይበሳጭ እና በድሎት ለተቀመጠ ፈጽሞ አይኾንም፤ ይጎረብጣል። እውነትም መንፈሱንም ሊያሽብረው ይችላል። እኔም የእርሳቸውን ቃል በመዋስ እላለሁ፤ በኢትዮጵያ ኹኔታ የደላው ካለ አይደለም ስለ መጽሐፉ ስለ ፕሮፌሰር መስፍንም እንኳ ባይሰማ ይሻለዋል፣ የማይበሳጭ ካለም ስለኢትዮጵያ ታሪክ አመጣጥም ኾነ አሁን ላለችበት ትርጓሜ ቁብ ሊሰጥ የማይችል ነው እና አርፎ ይቀመጥ፡፣ በተለይ ይህ መጽሐፍ ባስቀመጣቸው ተግዳሮቶች ።

ፕሮፌሰር መስፍን የአደባባይ ምሁርነትን በመምራት የሚስተካከላቸው ያለ አይመስለኝም። ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ምሁራን መካከል እንደ እርሳቸው የኾነ ምርታማ ጸሐፊ ፈልጎ ማግኘትም ከባድ ነው። በሦስት መንግሥታት ዳር ላይ ቆመው የትችት ዱላቸውን ሲሰነዝሩ ቆይተዋል። በማይዛነፍ እና የሐሳብ ተከታታይነት ባለው ጽሑፋቸውም ብዙ መጻሕፍቶችን እና፣ በየጊዜው በጋዜጦች እና በመጽሔቶች እንዲሁም በጆርናሎች ላይ ታከተኝ ሳይሉ ሐሳባቸውን ሲያንጸባርቁ ኖረዋል። "አነጋጋሪ" የሚል ቅጥያም ከተሰጣቸው ከርመዋል።

አንዳንዶች በተጨባጭ ማስረጃ ማቅረብ ባይቻላቸውም እርሳቸውን እንደሚጠሉ ይናገራሉ። የሚያምኑበትን ከመናገር እና የመሰላቸውን ሐሳብ ከመግለጽ አለመቆጠባቸው ምናልባት ከአድርባዮች ጎራ ስለማያሰልፋቸው፤ አልያም ከአንዱ ወገን ኾነው ሌላውን ለመጥላት የሚመች ባሕርይ ስለሌላቸው ይኾናል ከሁሉም አቅጣጫ የጥላቻ አስተያየት የሚሰነዘርባቸው። ከጥቂቶች በቀር ለጎንታይ ሐሳባቸው መልሶ ጎሻሚ ሐሳብ ይዞ የሚመጣ የለም። በአዲስ ነገር ጋዜጣ ላይ ሞክሼያቸው መስፍን ነጋሽ "ፕሮፍ ምን ነካቸው?" ብሎ ሁለት ተከታታይ ጽሑፍ ማቅረቡን ያስታውሷል። ሌሎችም ካሉ አንባቢያን ጨምሩበት።

ፕሮፌሰሩ መጽሐፋቸውን ሲጀምሩ አስደንጋጭ እና ቀልብ ሳቢ የኾነውን "መክሸፍ" የሚል ቃል ከማብራራት ይጀምራሉ። ለእርሳቸው መክሸፍ ማለት ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ የቀረ ኹነት፤ እንቅፋት ገጥሞት ሳይሳካ እና ሳይቀጥል የቀረ ታሪክ ማለት ነው ባጭሩ። እንደርሳቸው አመለካከትም መክሸፍ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለብዙ ዓመታት ግዙፍ ስፍራ ይዞ የቆየ ነገር ነው። ያውም አንድም እንኳ የታሪክ አጥኚ ዞር ብሎ ሳያየው።

ፕሮፌሰሩ በዚህ መጽሐፍ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት እና በሁዋላ የነበረችውን/ያለችውን ኢትዮጵያ ይዳስሳሉ። አብዛኞቹ የታሪክ ተመራማሪዎች እና ሊቃውንት ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ሲጽፉ ወደኋለኛው ዘመን መመለስ አይሹም። አንድም በመረጃ እጥረት አሊያም በዘመናዊ ትምህርት የተካኑት ሰዎች ስለ ኢትዮጵያ ቀይደው ያበጁት አተረጓጎም ለጉሞ ስለሚይዛቸው።





ፕሮፌሰር መስፍን ግን ከሁለት ሺሕ ዓመት በፊት እና በኋላ ያለችው ኢትዮጵያ በሥልጣኔ እና በኋለቀርነት ምን ትመስላለች የሚለውን አንስተው ይዳስሳሉ። "ያኔ ሥልጡኖች የነበረነው እንዴት ነው? ዛሬስ የኋላ ቀሮች መጨረሻ ለመኾን የበቃንበት ምክንያት ምንድነው?" በሚል ጥያቄ ላይ ተመስርተው ተንኳሽ እና አመራማሪ ጥያቄዎችን ይሰነዝራሉ። የድንጋይ መሥራት ጥበብ የታየባት ኢትዮጵያ ከትውልድ ወደ ትውልድ በደሳሳ ጎጆ የሚተላለፍ ባህል ለማዳበር የበቃችውስ ለምንድነው? ሲሉም ይጠይቃሉ።

ጥንት በኢትዮጵያ የታየው የሥልጣኔ ጅምር ዛሬ ካለችው ኢትዮጵያ ጋራ አልጣጣም ያለበት ምክንያት ተጀምሮ ያላለቀ ታሪክ ስላለን እና ክሽፈት ስለተጠናወተን ነው ባይ ናቸው። ፕሮፌሰር መስፍን የሚያነሱት ሐሳብ ስለ ኢትዮጵያ መልሰን መላልሰን እንድናስብ እና መነሻችን እና መድረሻችን ሳይጣጣም የቀረበትን ጉዳይ ልብ ብለን እንድናስተውል የሚያስገነዝብ ነው።

የዚህን የኋላ-ቀርነት መጨረሻ እና የታሪክ ክሽፈት እንዲገልጽላቸው ኤድዋርድ ጊበን የተባለው እንግሊዛዊ የታሪክ ጸሐፊ ያለውን ይጠቅሳሉ። "ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ዓለም ረስተውት ለአንድ ሺሕ ዓመታት ያህል አንቀላፉ፤" የታሪክ ጸሐፊው ይህን ያለው የሥልጣኔ ርምጃችን ከሽፎብን ቁልቁለቱን ስንወርድ ዐይቶ ነው" ሲሉም ያስረግጣሉ።

ኢትዮጵያውያን አሁን ላለንበት ሁኔታ የተዳረግነው በታሪካችን ውስጥ ያጣነው እና ሳንገነዘብ ያለፍነው ነገር የቱ ላይ ነው የሚለው በብዙዎች ውስጥ የሚመላለስ ጥያቄ ነው። ይህ ጥያቄ ኢትዮጵያ ውስጥ ተወልደው ላደጉ እና ዘር ማንዘራቸውን ሲጠይቁ ከዚያች ምድር መፍለቃቸው ለሚገባቸው ሁሉ እንቆቅልሽ ኾኗል። "ኢትዮጵያ" ስንል በየትኛዋ "ኢትዮጵያ" ላይ ነው የምንነጋገረው የሚለው ሐሳብ የተለያየ ትርጓሜ ስለተሰጠው አብዛኞቹ መስማማት ሳይችሉ ማዶ ለማዶ ኾነው እየተታኮሱበት ነው። ሩቅ እንኳ ሳንሄድ የንጉሡ ኢትዮጵያ፣ የደርግ ኢትዮጵያ፣ እና የኢሕአዴግ ኢትዮጵያ መልካቸውም ግብራቸውም ልዩ ልዩ ነው። እንደየመልኩ ተቀይደው ያሉትም ብዙ ናቸው።

ለፕሮፌሰር መስፍን ግን ጥንታዊት ኢትዮጵያ ራሷ በአግባቡ አልተገለጠችም፤ ወደ ኋላ ተመልሶ ያያት የታሪክ ተመራማሪም ኾነ ሊቃውንት የለም። የታሪክ አዋቂዎች እና ሊቃውንትም ከመካከለኛው ዘመን ተነስተው የጻፉልን የኢትዮጵያ ታሪክ ሙሉ ሥዕል አያሳይም የሚል አንደምታ ያለው ክርክር ያነሳሉ። የታሪክ አዋቂዎች እና ተመራማሪዎች የኋለኛውን የኢትዮጵያን ታሪክ አንዳንዱ 'ተረት' ነው፤ ሌላውም 'አፈ-ታሪክ' ነው በሚል መነሻ ከሺሕ ዓመታት ወዲህ ባለው ላይ ማተኮራቸው እሙን ነው። ይህ ዐይነቱ የታሪክ አቀያየድ የመጣው ደግሞ ታሪክ ጸሐፊዎቹ "ቈሳራውያን ሐይሎች" ቀደው በሰፋት ኢትዮጵያዊነት ላይ በመመሥረቱ ነው የሚል መከራከርያም ያቀርባሉ። ኢትዮጵያውያን የታሪክ ጸሐፊዎች ትክክለኛውን የኢትዮጵያን ታሪክ ከምንጩ እንዳልቀዱት እና ለቈሳራውያን ሐይሎች በሚስማማ መንገድ ጽፈውታል፤ ስለዚህ ታሪክ ውሉን ስቷል ሲሉም ይሞግታሉ።

ለእርሳቸው ይህ ዐይነቱ የታሪክ አጻጻፍ ወይም አዘጋገብ አንድም ለእንጀራ ሲባል አሊያም ቁሳራዊ ሐይሎችን ለማስደሰት ከሚደረግ ትግል የሚመነጭ ነው። በዚህ መጽሐፍ ፕሮፌሰር መስፍን ያነሱት ጭብጥ ውኃ አያነሳም የሚባል አይደለም። ክርክራቸው ውሃ የሚያነሳበት ዧነኛ ጉዳይ ስለ ኢትዮጵያ ስንነጋገር ስለ አክሱም ማንሳታችን የማይቀር በመኾኑ ነው። ስለ አክሱም ስናወራ ደግሞ ከሁለት ሺሕ ዓመት በፊት ስለነበረ ሥልጣኔ እያወራን ነው፤ አንድም አክሱም በኢትዮጵያ ምድር ላይ ከሰማይ ተውርውሮ የተተከለ የተዐምር ድንጋይ ነው ብለን ራሳችንን ካላሳመንን በቀር ወይም ለዚያ ሥልጣኔ አበርክቶት የነበራቸው ሌላ ሕዝቦች ናቸው የሚል በቂ ማረጋገጫ እስካለገኘን ድረስ ንብረትነቱም ኾነ ታሪኩ የኢትዮጵያ ከመኾን አያመልጥም። ስለ አንዲት አገር በቂ የኾነ መነሻ ከሌለን ስለመድረሻዋ መጨቃጨቁ ጉንጭ አልፋ ከመኾን የሚዘል አይመስለኝም። ፕሮፌሰር መስፍንም የሚሉት የኢትዮጵየ ታሪክ ቁንጽል በኾነ መንገድ በመነገሩ "ክሽፈት" ኾኗል ነው። እስኪ ነገራቸውን ለማስረገጥ እና በማስረጃ ለመጥቀስ፣ ለትክክለኛ ታሪክ ትርጓሜ





የሰጡበትን ምዕራፍ እንመልከት፤ በተጨማሪም ኢትዮጵያዊ ታሪክ ማለት ምን ማለት እንደኾነ ያዩበትንም እንይ።

ትክክለኛ የታሪክ ትርጓሜ የሚሉትን እንዲህ ያስቀምጡታል:--

"ታሪክ የሕዝብ፤ የተከታታይ ትውልዶች ሥራ ነው፤ ኑሮ ነው፤ ትግል ነው፤ ተጋድሎ ነው፤ እያንዳንዱ የቀደመው ትውልድ ኀብረቱን፣ ንብረቱን እና መብቱን፤ በአጠቃላይ የአብሮ መኖር ሕልውናውን አረጋግጦ ለሚቀጥለው ትውልድ ያስተላልፈውንና ያስተላለፈበትን ኹኔታ ጭምር የሚገልጽ ቅርስ ነው። ተከታዩ ትውልድ ከቀደመው ትውልድ የተረከበውንና ራሱ ደግሞ የጨመረውን እያካተተ የሚተርክ ዘገባ ነው። የኋለኛው ትውልድ ባለፉት ትውልዶች መስዋእትነት በተጣለው መሠረት ላይ የተሻለ፤ የጠነከረ እና የበለጸገ ማኅበረሰብ ለማነጽ የሚያደርጉትን ጥረት ካለፈው ጋራ የሚያስተያይ መዝገብ ነው። ትውልዶችን ከትውልዶች ጋራ የሚያስተሳስር እና የሚያገናኝ ሰንሰለት ነው።" ይህ የማያከራክር ሳይንሳዊ የኾነ አጥጋቢ ትርጓሜ ነው።

ይህን ካሉ በኋላ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ታሪክ ማለት ደግሞ እንዲህ ነው ይላሉ።

> "ለኢትዮጵያውያን ታሪክ ማለት ሁልጊዜም ከእግዚአብሔር ፈቃድ እና ፍቅር ወይም ጥላቻ ጋራ የተያያዘ ነው። በሃይማኖተኛ ማኅበረሰብ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ጎልቶ መውጣቱ አያስደንቅም። የሚያስደንቀው የሰው ልጅ ገና ከሕጻንነት መውጣት አለመቻሉ ነው። ከሕጻንነት አልወጣም ማለት ራሱ ለሚሠራው ሁሉ ገና ሐላፊነት መውሰድ አልጀመረም ማለት ነው። ያጠፋውንም ያለማውንም የአምላክ ፈቃድ ስለሚያደርገው ለስህተቱም ኾነ ለጥፋቱ ተጠያቂ እንዳይኾን ያደርገዋል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ኾኖ ነው ከተባለ ማንም ሊከራከር አይችልም።"

ይላሉ። ይህ ደግሞ እምነትን መሠረት ያደረገ አምጪውም ፈጪውም የማይጨበጠው አምላክ ነው በሚል መደምደሚያ ላይ የቆመ ነው።

እንግዲህ ፕሮፌሰር መስፍን የታሪክን ትክክለኛ ትርጓሜ ካስቀመጡበት ኹኔታ አኳያ ስንመለከተው ኢትዮጵያውያን ታሪክን የሚያዩበት ዐይን ከእግዚአብሔር ፈቃድ፣ ፍቅር እና ጥላቻ ጋራ በመተሣሰሩ ከጅምሩ ቅኝቱን የሳተ ነው። ለክሽፈቱ ጅምርም ይኼው አጠቃላይ የኾነ የታሪክ ግንዛቤ ይኾናል። ምንም እንኳ ለእርሳቸው በሃይማኖተኛ ማኅበረሰብ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ጎልቶ መውጣት ባያስደንቃቸውም። አስደናቂው ነገር ግን የሰው ልጅ ከሕጻንነት መውጣት አለመቻሉ ነው። በርግጥ ታሪክን በዚህ ግንዛቤ የሚወስድ ማኅበረሰብ ከሕጻንነት ሳይወጣ ሐላፊነት ላለመውሰድ የሚንገታገተው ለምንድን ነው? የእግዚአብሔር ጎልቶ መውጣት በራሱ ከሕጻንነት ላለመውጣት ብቸኛው ምክንያት አይደለም ወይ? የሚል ጥያቄን ያጭራል። ፕሮፌሰር መስፍን የእግዚአብሔር ጎልቶ መውጣት ላይ በዝርዝር አልሄዱበትም። ካስቀመጡት ትክክለኛ የታሪክ ትንታኔ እና ትርጓሜ አንጻር ታሪክ የሰው ልጆች የሥራ ውጤት ነው። ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ መዝገብ ነው። ትውልድ እና ትውልድን የሚያስተሳስር ሰንሰለትም ነው። በዚህ ትርጓሜ ከተስማማን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ ፈቃድ እና ጥላቻው ጣልቃ እንዲገባ መፈቀዱ እና መወሰኑ አሁን ላለው ኋላ-ቀርነት አስተዋጽኦ ማበርከቱን በዝርዝር ያዩት አልመሰለኝም። አንድም ሃይማኖታዊ የኾነውን ማኅበረሰብ ለመጎነጥ በዚህ ሰዓት አልፈለጉም ወይም ከዋናው መሠረታዊ ችግር ይልቅ "በሕጻንነቱ" እና በሐላፊነት አልሸከም ባይነቱ ላይ ማተኮርን መርጠዋል።

በዘመናዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ ከላይ ምንም ዐይነት ሥልጣን የሌለበት ሥርዐተ-መንግሥት ለማቋቋም በመጀመርያ ቤተ ክርስቲያን እና ሀገረ-መንግሥት መለያየት አለባቸው የሚለው ገዢ ሐሳብ ኾኖ ያገለግላል፤ ይሠራበታልም። ፍትህን ለማስፈን እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዐትን በማንኛው ሰብዐዊ ፍጡር መካከል ለማጎናጸፍ አንደኛው መደረግ ያለበት ነገር ነው ተብሎ





ይታመናል። ርግጥ ነው የቤተ ክርስቲያን እና የሀገረ-መንግሥት የጋብቻ ፍቺ በብዙ አገሮች ላይ ገና ነጥሮ ያልወጣ ጉዳይ ነው። በተለያየ እና ውስብስብ በኾነ መንገድ ተጽእኖውን ከማሳረፍ አልጸዳም፤ በዴሞክራሲ ብዙ ተጉዘናል በሚሉት አገሮችም ጭምር። ኢትዮጵያ ውስጥ ችግሩ ሥር የሰደደ እንደኾነ የሚያሳየው ግን ፕሮፌሰር መስፍን 'ኢትዮጵያውያን ሃይማኖታዊ ማሕበረሰብ ናቸው እናም ታሪክ የሚታየው በእግዚአብሄር ፈቃድ፣ ፍቅር እና ጥላቻ መስመር ነው' ብለው ባስቀመጡት ላይ የቆመ በመኾኑ ነው። ስለዚህ የትርጓሜ ፍቺው ካልተቀየረ በቀር ከተመሠረተበት ተነቅሎ "ሕጻንነቱ"/ሐላፊነት ለመሸከም ፈቃደኛ መኾን አለመቻሉ ሁለተኛ ነገር ይኾናል። ይህን ጉዳይ አንድ ቀን አስፍተው እንደሚመጡበት ተስፋ አድርጌ ልለፈው።

ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ክሽፈት ሲያትቱ አንቱ የተባሉትን የታሪክ ሊቃውንቶች ያነሳሉ። ከእነዚህም መካከል ሦስቱን በዋነኛነት ከእነሥራዎቻቸው ይጠቅሷቸዋል። ፕሮፌሰር ስርግው ሐብለሥላሴን፣ ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራትን እና ፕሮፌሰር መርዕድ ወልደአረጋይን።

እነዚህ ፕሮፌሰሮች በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የጻፉ እና ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ በተነሳ ቁጥር በቅድሚያ የሚጠቀሱ ሰዎች ናቸው። ፕሮፌሰር መስፍንም የኢትዮጵያን ታሪክ ክሽፈት ሲዳስሱ በእነዚሁ ሊቃውንት ሥራዎች ላይ በመንተራስ "ምን ዐይነት ኢትዮጵያ ነበር ያሳዩን?" ሲሉ በዝርዝር ይጠይቃሉ።

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኹት የመጀመርያ መነሻቸው ያደረጉት የኢትዮጵያ የታሪክ ሊቃውንት ኢትዮጵያን ያዩበት መነጽር የተንሸዋረረ ወይም ቅኝቱ ቄሳራዊ በኾነ አስተምህሮ የተለወሰ ነው በሚል ነው። ወደ አገራዊ ሊቃውንቶች ከመምጣታቸው በፊት ስለ ቄሳራውያን ምሁራን ጽፈዋል። "ቄሳራውያን ምሁራን ስለኢትዮጵያ የጻፉት አብዛኛው ነገር ለእነርሱ በሚገባቸው እና በሚያመቻቸው መንገድ ነው። እነርሱ ስለ እኛ ሲጽፉ እኛም ያለምንም ጥያቄ ጥቁር ሰሌዳ ኾነን እንቀበላለን። አስቀድሞ አብዛኛው ቄሳራዊ ምሁር የኢትዮጵያን ታሪክ የሚጽፈው የተላከበትን አገር ፖለቲካዊ ጥቅም ለማስጠበቅ

ነው።" ይላሉ። ይህ በርግጥ የተረጋገጠ እውነት ነው። ኢትዮጵያውያን ምሁራንም እነርሱ በቀደዱላቸው ቦይ በመፍሰሳቸው የክሽፈት ታሪክ ለመጻፍ ምክንያት ኾነዋል የሚል ነው የመከራከርያ ነጥባቸው። ለዚህም እንደማስረጃ ከሚያቀርቡዋቸው ነገሮች መካከል የፕሮፌሰር ታደሰ ታምራትን እና የፕሮፌሰር መርዕድ ወልደአረጋይን የተሸማቀቀች/የተኮማተረች ኢትዮጵያ ካርታ እንደምሳሌ በመጥቀስ እና ከመጽሐፉ ጀርባ በማስቀመጥ ነው።

በመጽሐፉ ላይ ካርታ ብቻ በማስቀመጥ ሳይኾን የእያንዳንዳቸውን መጽሐፍ በመጥቀስ በውስጣቸው በአግባቡ ስላልተተረጎሙ የእንግዚዝኛ ቃላቶች ሁሉ ትችትን ይሰነዝራሉ። "ስቴት" የሚለውን ቃል እንደ ቁልፍ ቃል ሳይኾን እንደ ተራ ቃል ችላ ብለው ማለፋቸው ተገቢ እንዳልኾነም ጽፈዋል። "ስቴት" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ዋና ትርጉሙ "ከበላዩ ምንም ሥልጣን የሌለበት ሀገረ-መንግሥት ነው" ይላሉ። መርዕድም ኾኑ ታደሰ በመጻሕፍታቸው/ጽሑፋቸው ውስጥ ኢትዮጵያ የተዋሃደች ስቴት ነች አይደለችም የሚል ጥያቄ ያነሳሉ። መዋሃድን የስቴት መሠረታዊ ባሕርይ አድርገውም የተቀበሉት ይመስላል ይላሉ። ይህ ትንታኔ በተለይ በዐሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመርያ እና ከዚያ በፊት የሚሠራ ነው ወይ ነው? ጥያቄያቸው። የተዋሃደ እና ያልተዋሃደ ስቴት ማለትስ ምን ማለት ነው? ሲሉም ይጠይቃሉ።

በተቃራኒው "ኢስላም በኢትዮጵያ ውስጥ" የሚል መጽሐፍ የጻፈው እንግሊዛዊ ሊቅ ትርሚንግሃም ከሁለቱም በተሻለ መንገድ "ስቴት" በኢትዮጵያ ከሕዝብነት በላይ መኾኑን አስቀምጧል ባይ ናቸው። ዝርዝሩን እዚህ አልጠቅሰውም አንባቢያን ከመጽሐፉ ታገኙታላችሁ።

የፕሮፌሰር የመከራከርያ ነጥብ ግን ትርሚንግሃም በኢትዮጵያ ነጥሮ እና ተረጋግጦ የወጣውን የኢትዮጵያውያንን ሕዝብነት የበለጠ ተረድቶታል ነው። በውስጡ የታመቀ የከፋፍለህ ግዛ ሐሳብ ማዘሉ እንዳለ ኾኖ። በተመሳሳይ በሦስቱም ሊቃውንት ጽሑፎች ውስጥ ሌላኛው አከራካሪ ቃል "ኢምፓየር" የሚለው





ነው። በቁም ትርጉሙ ኢምፓየር በውስጡ ሁለት ዓይነት ሥርዐትን የያዘ የፖለቲካ ድርጅት ነው። አንዱ የቅኝ ገዢው (ኢምፔሪያል) አገር (ስቴት) በራስ አገር ላይ ያለው መንግሥት ሲኾን ሌላው ደግሞ በቅኝ አገዛዙ ስር ባሉት ሕዝቦች ወይም ግዛቶች ላይ ያለው ነው። ስለዚህ ከዚህ ትርጓሜ ተነስተን ስናየው ኢትዮጵያ በየትኛው ክፍለ ዘመን ነው ይህን ዐይነት አስተዳደር የነበራት የሚለውን ጥያቄ እንድናነሳ እንገደዳለን። በእኔ አመለካከት ፕሮፌሰር መስፍን እነዚህ ትልልቅ ጽንሰ ሐሳብን ያዘሉ ቃላቶች በኢትዮጵያ ታሪክ ትንታኔ ውስጥ መቀመጣቸው ታሪክን በተዛባ መንገድ እንድንረዳው ምክንያት ይኾናል ማለታቸው አግባብነት ያለው ነው ተብሎ ቢወሰድ ሊቃውንቱን በግል ወደማጣጣል የሚሄድ ሳይኾን አሁን ያሉትም ኾኑ ወደፊት የሚመጡት የታሪክ ሊቃውንት መስመር እንዲያሲይዙት የሚያደርግ የማንቂያ ደወል እንጂ አንዳች የጥላቻ/ የማጣጣል መንፈስን ያዘለ አይደለም።

ፕሮፌሰር መስፍን ፕሮፌሰር ስርግውን በተሻለ ዕይታ ከጥቂት የፖለቲካ እና የእንግሊዝኛ ቃላት ችግር ውጭ አመስግነዋቸዋል። እንዲያውም መጽሐፋቸው እና ጽሑፎቻቸው በአማርኛ ተተርጉመው ቢቀርቡ መልካም መና እንደሚኾኑም ተናገረዋል። ፕሮፌሰር ታደሰ ላይ ግን ሰፋ ያለ ትችትን አቅርበዋል። የታደሰን "ክርስቲያን ኢትዮጵያ" ሽምቃቃነት አጉልተው ለማሳየት ሰፋ ያለ ትንታኔ ሰጥተዋል። በፕሮፌሰር መርዕድ ጽሑፍ ላይ አጠር ያለ ትችት ሰንዘረዋል። ከዚህ በሁዋላ የተሻገሩት ቄሳራውያን ሐይሎች ከዐፄ ዮሐንስ እና ከዐፄ ምኒልክ ጋራ ስላደረጓቸው ውሎች እና በድንበር ማስከበር ጉዳይ እና የቅኝ ገዢነት በኢትዮጵያ እንዳይስፋፋ ስለተደረገው ተጋድሎ ነው። ከዚያም የኢትዮጵያ ተሀድሶ ብለው ከዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን አንስተው ኢትዮጵያን ለመውረር ያሰፈሰፉት የቄሳራዊ ሐይሎች እንዴት ባለ አኳኋን ስውር ደባቸውን ሲሠሩ እንደከረሙ እና ኢትዮጵያ የተኮማተረች እና የተሸማቀቀች ለመኾን እንደተዳረገች በዝርዝር ጽፈዋል። በጊዜው በቄሳራዊ ሐይሎች እና በኢትዮጵያ

ነገሥታት መካከል የተደረጉትንም ውሎች በመጽሐፉ ውስጥ አካተዋል:: ለአንባቢ ፍርድ ይመች ዘንድ::

በዚህ ዝርዝር ውስጥ አንድ የተለየ ምልከታ ይዘው መጥተዋል:: ኢትዮጵያ የመቶ ዓመት ታሪክ ነው ያላት የሚል ክርክራቸውን ለፖለቲካ ትርፋቸው የሚጠቀሙበት የዘመኑ ፖለቲከኞች ስለመስፋፋት ሲያነሱ ዕዳውን የሚያሸክሙዋቸው እና ቅጽሉን የሚለጥፉላቸው በዐፄ ምንሊክ ላይ ነው:: የአንድነት ሐይሉ የምንሊክ ደጋፊ፣ የጭቆና ሰለባ ኹኛለሁ የሚለው ሌላው አካል ደግሞ የምንሊክ ጠላት ኾነው ተሰልፈዋል:: ይህ የመስፋፋት ጉዳይ ተፈጽሟል የሚባል ከኾነ (የኢትዮጵያ ግዛት እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ድረስ ነበር ብሎ ለሚያምን አይሠራም) የተፈጸመው በዐፄ ዮሐንስ ዘመን ነው ብለው ጥቁምታ ሰጥተው ያልፋሉ:: ምክንያታቸውም ምንሊክ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ አራተኛ ሥር የሚተዳደር የሸዋ ንጉሥ እንጂ ንጉሠ ነገሥት አልነበረም እና ነው የሚል ነው::

ፕሮፌሰር መስፍን ያነሷቸውን አብዛኞቹን ጉዳዮች በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ ዘርዝሮ ማቅረብ አይቻልም:: ነገር ግን እኔም ወደ ጹሑፌ ማጠቃለያ ለመንዝ በመጽሐፉ መጨረሻ ግድም ስለ "ኢትዮጵያዊ እውነት" ያሉትን ጠቅሼ ላብቃ:: "ኢትዮጵያዊ እውነት ማለት ወረት ማለት ነው፤ ይህን ሐቅ መቀበል ካልቻልን ተስፋ የለንም::" {ይህን ከማለታቸው በፊት ያስቀመጡትን ዝርዝር በቀደመው የፌስ ቡክ ፖስቴ ላይ ይፈልጉት} ካሉ በኋላ "እውነት ሁለት መሠረቶች አሉት፤ አንዱ እምነት ነው አንዱ እውቀት ነው:: ከእምነት የሚነሳውን እውነት የተገለጠ እውነት ልንለው እንችላለን፤ ከእውቀት የሚነሳው ደግሞ የተረጋገጠ እውነት ይባለል:: በተገለጠ እውነት የሚመሩ ማሕበረሰቦች ባህላዊ ይባላሉ:: በተረጋገጠ እውነት የሚመሩ ደግሞ ሳይንሳዊ ይባላሉ፤ በእውቀት የሚመሩ ማለት ነው:: . . . በተገለጠ እውነት ላይ ጥያቄ ወይም ክርክር ማንሳት ፍጹም አይቻልም፤ ወይም አምኖ መቀበል ነው፤ ወይ አለመቀበል ነው:: መመራመር የትም አያደርስም፤ ኢትዮጵያ የተገለጠ እውነት አገር ነች ማለት እንችላለን::" ይላሉ::





እንግዲህ ኢትዮጵያ እንደ አገርም ኾነ እንደ ሕብረተሰብ በተረጋገጠ እውነት (ሳይንሳዊ በኾነ) ላይ ካልተመሠረተች ያልከሸፈ ታሪክ ባለቤት መኾን እንደምን ይቻላታል? ይህ ፕሮፌሰር መስፍን ያነሱት የመክሸፍ ነገር የእያንዳንዳችንን መንፈስ የሚኈጉጥ ነው:: ቆመንበታል የምንለውን የእውነት መሠረትም የሚያናጋ ነው:: በተለይ በተረጋገጠ እውነት ላይ ከመቆም ይልቅ በተገለጠ እውነት ላይ ላለን ሰዎች ተግዳሮቱ የበዛ ነው:: ምናልባት ካንዱ እውነት ወደ ሌላኛው እውነት ለመሻገር የሚፈጀውን ጊዜ እያሰብን የምንባክን ሰዎች ካለን ደግሞ ሕመሙ ጋኤናችንን እስከማስጮህም ድርስ የበረታ ይኾናል:: ክሽፈቱ እውነትን አለው፤ እውነትን ለመቀበል እንደሚያስቸግረው ሁሉ ትግሉ ትልቅ ትንቅንቅን ይጠይቃል:: ክሽፈት እና እውነት እኩያ እና መንትያ ሲኾኑ ደግሞ አይጣል ነው:: ቁም! ክሽፈትህን እወቅ! ክሽፈትህን እመን! ያኔ ቁም ባዩን አታገኘውም::

*******************************************

ትችት አራት በታምራት ነገራ

ነብር ዥንጉርጉርነቱን ኢትዮጵያዊ ክሽፈቱን

"ክሽፈት እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ" የተሰኘው አዲሱ የፕሮፌሰር መስፍን መጽሐፍ በሕይወቱ ካነበበኋቸው መጻሕፍት መካከል አእምሮዬን ብቻ ሳይኾን መንፈሴንም ጭምር ማነጋገር ከቻሉት ጥቂት መጻሕፍት ውስጥ እመድበዋለሁ:: ይህ ለምን ኾነ? ስለማንነቴ በተለይም ስለኢትዮጵዊነት፤ ስለሐበሻነት፤ ስለኦሮሞነት፤ ስለጥቁርነት፤ ስለስደተኝነት፤ ስለ ሥነቋንቋ፣ ስለስኬት እና ስለሌሎችም ተጓዳኝ ጉዳዮች በጥልቁ እንዳስብ ሕይወት አስገዳጅ ጥያቄ ባቀረበችልኝ ወቅት የደረሰኝ መጽሐፍ በመኾኑ ነው:

ከአገር ከወጣሁበት ጊዜ ጀምሮ አንዳንዴ በስደት ወሬ፣ አንዳንዴ በትምህርት ወሬ፣ ሌላ ጊዜ በብስጭት፣ አንዳንድ ጊዜ

ደግሞ በሥራ ወሬ ጊዜ ከማጥፋት ነገሮች ቀስ በቀስ በሕይወቴ እየሰከኑ ነው። ለምን ከአገር ወጣኹ? ለምን አልታሰርኩም? ለምን እስከመሞት ድርስ ለመቆየት ወኔ ከዳኝ? የሚሉትን ጥያቄዎች አሁን ብቻ ሳይኾን ዕድሜ ልኬን የምጠይቃቸው ናቸው። በተለይ አዲስ ነገርን አብረን ፀንሰን፤ አብረን ወልደን፤ አብረን አሳድገን፤ አብረን ሞት ከፈረድንባት ወዳጆቼ ጋራ እነዚህን ጥያቄዎች ለዕድሜ ልክ ደግመን ደጋግመን ማንሳታችን የሚቀር አይመስለኝም።

በስደት ሕይወት ከገጠመኝ ማንኛውም መንከራተት ይልቅ ነፍሴን የሰነጣጠቃት ግን ለመሰደድ መወሰኔ ያስከተለውን ጣጣ ማወቄ ነው። ይህን ጣጣ በሚገባ ለመገንዘብ ባልሳሳት አንድ ዓመት ፈጅቶብኛል። **ቢያንስ ነፍስ ካወቅኹበት ጊዜ ጀምሮ ዓላማዬ ብዬ የያዝኩት ፖለቲካዊ ሕይወት ለካ ከበቀለበት አፈር ሲወጣ** ምንም ትርጉም የለውም። አዲስ ዓላማ በአዲስ አገር እንዴት ይፈጠራል? አዲስ ዓላማ በባዕድ ቋንቋ ምን ማለት ነው? የሚሉ መሠረታዊ የትርጉም ጥያቄዎች እስኪበቃኝ ናጡኝ። መናጡ ሲረጋጋ የተረፈኝ ድፍድፍ ከትውስታ ቋንቋ፣ ከናፍቆት እና ከዕድሜ ንባብ ጋር የተለወሰ በመኾኑ ገና ለብዙ ዘመን የማነጥረው ቁም ነገር ይኾናል ብዬ አስባለኹ።

ከዚህ በኋላ መናጡ እየቀረልኝ ቢኾንም፤ የተሰነጠቀችው ነፍሴ ግን መልሳ አልተጠገነችም። ብርሴ ብቻ ሳይኾን ነፍስም ከነቃች ወደኋላ አትመለስም። ከነፍሴ ስንጥቅ ውስጥ ከስንት አንዴ ፍንቅል እያለ የሚወጣው ትዝታ እና አንዳንድ ጥልቅ ሐሳብ ግን እንደ ቅዠት እያባነነ ሊፈረካክሰኝ ሲተናነቀኝ አገኘዋለኹ፡

የፕሮፌሰርን መጽሐፍ ሳነበው ከስድሳ ዓመታት በላይ ኢትዮጵያን አሻሽላለኹ፤ ለሕዝቤ አገለግላለኹ ብላ የምትታገለው ነፍሳቸው በራሷ ጉዞ የገጠማት ስንጥቅ ታየኝ። ከዚህ የነፍሳቸው ስንጥቅ የሚወጣውን መልዕክት መዓዛ ደግሞ በደንብ አውቀዋለኹ። "በእኔ ዕድሜ ያደኩበት ሰፈር ስም፤ የተማርኹበት ተማሪ ቤት ስም፤ ያስተማርኹበት ተማሪ ቤት ስም፤ የሠራኹበት መሥሪያ ቤት ስም ተለውጧል። ስለዚህ እኔ የሌለ ሰፈር አድጌ፤





የሌለ ተማሪ ቤት ተምሬ፤ የሌለ ተማሪ ቤት አስተምሬ፤ የሌለ መሥሪያ ቤት ሰርቼ፤ የሌለ ዩኒቨርስቲ አስተምሬ ... እኔ በጡረታ መኖሬ ያስገርማል! ከሽፎ የከሸፈ ኑሮ መኖር እንበለው!" ፕሮፌሰር መስፍን መልካሙን ገድል ተጋድያለኹ ማለት በሚገባቸው የሕይወት ዘመናቸው ላይ 'ከንቱ! ሁሉም ነገር ከንቱ!' የሚሉ አይመስልምን? ነፍስ ስትሰነጠቅ እውነት እውነቱን እንዲህ ታናግራለች።

ይህ ማለት መጽሐፉ አላስፈላጊ በኾነ፤ እንዲያውም በፕሮፌሰር መስፍን ማዕረግ ላለ የአደባባይ ምሁር ሊመጥኑ በማይችሉ አላስፈላጊ ሐሳቦች አልተጥለቀለቀም ማለት አይደለም። የፕሮፌሰር መስፍን መልዕክት የሚቀርበው ለስድሳ ዓመታት ሲጠነስሱት፣ ሲያጠምቁት እና ለአደባባይ ሲያድሉት ከኖሩት የቀኝ ዘመም ፖለቲካ ጠላ ጋር ተደባልቆ ስለኾነ ብዙ ሰው መጽሐፋቸው ባዘለው መልካሙ መልዕክት መዓዛ ከመሳብ ይልቅ በዚህ ቀኝ ዘመም ጠላ ጠረን ብቻ ሊገፈተር ይችላል።ኢትዮጵያ ውስጥ የመጽሐፍ ሐሳብ ተቀብሎ፤ ለመጽሐፉ የቀብድ ገንዘብ ከፍሎ፤ ሐሳቡን ከጸሐፊው ጋር አዳብሮ፤ ለጸሐፊው አርታዒ መድቦ፤ ለአርታዒው የምርምር እና ለሌላም ሥራ የሚኾኑ አጋዥ ረዳቶች አዘጋጅቶ መጽሐፉን ከደራሲው ጋር የሚፀንስ፤ መጽሐፉን እንደ ደራሲው ኾኖ ለአደባባይ የሚያደርስ አሳታሚ የሚባል ነገር ጭራሹንም ስለሌለ፤ ለተወሰነው የመጽሐፉ ክሽፈት ተጠያቂው ያው የከሸፈው የኢትዮጵያ የኅትመት ኢንዱስትሪ ነው

በመጽሀፉ አላስፈላጊ ሐሳቦች እንዲስገሰጉ ሌላው ተጠያቂ ራሳቸው ፕሮፌሰር መስፍን ናቸው። ምሁራን መጽሐፍ ለማሳተም በሚያፍሩባት ኢትዮጵያ እስከ አሁን ድረስ በራሳቸው ጥረት (ብቻቸውን) ያለማቋረጥ እና ያለማንም ረዳትነት መጻሕፍትን በአማርኛ መጻፋቸው እጅግ አስገራሚ ቢኾንም፤ አሁንም ድረስ መጽሐፋቸውን አንድ ሁለት ዙር እንዲያነብላቸው፤ ከዚያም እንዲተችላቸው የሚፈቅዱለት ሰው እንዲኖር ማድረግ አለመቻላቸው ከራሳቸው "እኔ ስናገር ብቻ ስሙኝ" ከሚለው ባሕርያቸው የመነጨ ይመስለኛል። 'እስኪ ጽሑፌን እይልኝ፤ ከዚያም ይስተካከሉ እና ይብራሩ የምትላቸው ሐሳቦች ካሉም

ጠቁመኝ፤' ብሎ ጽሑፍን ለአርታኢ መስጠት ምሁራዊ ትህትና ይጠይቃል፡፡ ፕሮፌሰር መስፍንን ደግሞ በትህትና ማማት ትንሽ ይከብዳል፡፡

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ መጽሐፉን ሙሉ ለሙሉ መገምገም፣ መዳሰስ፣ ወይም መተቸት አይደለም፡፡ ስለዚህ በዚህ ጽሑፌ መጽሐፉ ውስጥ የተጀቦኑትን አላስፈላጊ እና አርቲ ቡርቲ ናቸው ብዬ የወሰድኳቸውን ሐሳቦች፣ ማስረጃዎች እና መከራከሪያዎች በሙሉ አልነካቸውም፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ ፕሮፌሰር መስፍን ሊያስተላልፉ የፈለጉት መልእክት በምዕራፍ አንድ ማለትም ከገጽ 7 እስከ 33 እና በምዕራፍ 12 መደምደሚያ፤ ማለትም ከገጽ 182 እስከ 202 ውስጥ በሚገባ ተካቷል፡፡ የተቀረው የመጽሐፉ ክፍል የተዘጋጀው እንደመልእክቱ ማስረጃ እና ለመልእክቱ ፍልስፍናዊ መሠረት ለማቅረብ ቢኾንም በዓላማው ፊጽሞ የከሸፈ በመኾኑ እንዳለ ተቆርጦ መጣል ነበረበት፤ ወይም እንደገና በሚገባ ተፈትኖ እና ታሽቶ መጻፍ ነበረበት፡፡ ፕሮፌሰር መስፍንን በአማርኛ ቋንቋ ምርጥ ከሚባሉ ጸሐፍያን የሚያስመድባቸው አንደኛው ነገር በጽሑፎቻቸው ትልልቅ እና ውስብስብ የሚባሉ ሐሳቦችን በቀላሉ፤ ያውም እጅግ ውብ በኾነ የቃላት አጣጣል የማስቀመጥ ችሎታ ስላላቸው ነው፡፡ ይህ የመጽሐፉ ክፍል ውበትም ኾነ የሐሳብ ጥራት ከማጣቱ የተነሳ ፕሮፌሰር መስፍን እንደልማዳቸው ከሥራቸው አረፍ ለማለት ለቡና ወደ ቶሞካ ጎራ ሲሉ ሌላ ሰው ጽፎ ያስቀመጠው ይመስላል፡፡ የዚህ መጽሐፍ ክፍል መበላሸት አሳዛኝ የሚኾነው፤ ፕሮፌሰር መስፍን ሊያስተላልፉ የፈለጉትን መልእክት በተገቢ እና ጠንካራ የመከራከሪያ ሐሳቦች እንዳይደገፉ በማድረጉ እና በዝባዝንኬ ዋናውን መልእክት እንዳያፍታቱ ጋሬጣ ኾኖ መገኘቱ ነው፡፡

መጽሐፉ ጥሩ አርታኢ ቢያገኘው ኖሮ የፕሮፌሰርን መልእክት በሚገባ የያዙትን ገጾች ብቻ በመምረጥ (እንደ *አሁኑ በመጽሐፍ መልክ* ሳይኾን) ሰፋ እና ጠንከር ያለ ዦርናል ጽሑፍ ይወጣው ነበር፡፡ የዚህ ጽሑፍ ትኩረትም በተጠቀሱት ገጾች ላይ በተሳካ ኹኔታ ተላልፏ ብዬ በማስበው መልእክት ላይ ማነጣጠር ብቻ ነው፡፡ ምናልባትም መጽሐፉን ማንበብ የሚፈልግ ሰው





እነዚህን ገጾች ብቻ መርጦ ቢያነብ የፕሮፌሰሩን መልእክት በሚገባ ያገኘዋል፡፡ እኔም ትኩረቴን እና ትንቅንቄን የማደርገው ከመጽሐፉ ዋነኛ ክፍል ጋር ብቻ ይኾናል፡፡

## *መክሸፍ እና ኢትዮጵያ በፕሮፌሰር መስፍን ዕይታ*

የፕሮፌሰር መስፍን የክሽፈት ትርጓሜ በሁለት ነጥቦች ላይ ያተኩራል፡፡ አንደኛ አንድ የተጀመረ ነገር የታቀደለት ግብ ጋር ሳይደረስ መቅረት፡፡ ሁለተኛ ጅማሮው ምንም እድገት ሳያሳይ እዚያው ባለበት እየተራመደ መቅረት፡ በፕሮፌሰር መስፍን ትርጓሜ መክሸፍን የሚያስከስተው ሌላው ምክንያት የተፈጥሮ ሕግ ነው፡፡ የመለወጥ የተፈጥሮ ሕግ፡፡ ይህን የተፈጥሮ ሕግ እንዲህ ያስቀምጡታል "ወደተሻለ ደረጃ ካልተለወጡ ወደባሰ ደረጃ መውረድ የማይቀር ነው፤ ወይም በሌላ አነጋገር ካላደጉ እና ካልተሻሻሉ መሸገት እና መበስበስ፤ በስብሶ መፈራረስ ግዴታ ነው፡፡" ገጽ10 ይህ የክሽፈት ትርጓሜ ብዙዎቻችንን ሊያስማማ ይችላል፡

በመቀጠል ፕሮፌሰር መክሸፍ በኢትዮጵያ ታሪክ ከፍተኛ ሥፍራ እንዳለው ያስረግጣሉ፡፡ ከዚህ የመክሸፍ ታሪክ የተረፈው ምናልባት ለአገር የመሞት ታሪክ ብቻ ሊኾን እንደሚችል ግምታቸውን ያስቀምጣሉ፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሕልውናን የማስረገጥ ረጅም ልምድ እንዳለ፤ ሌላው ነገር ሁሉ የሚከተለው ሕልውናን በማስረገጥ ላይ እንደኾነ ይናገራሉ፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሕልውናን ከማስረገጥ ባሻገር ያለውን የኢትዮጵያ የታሪክ ገዞ ሙሉ ለሙሉ ለማለት በሚያስደፍር መልኩ ፕሮፌሰር መስፍን የከሸፈ ብለውታል

ይህ የመጽሐፉ ክፍል ውበትም ኾነ የሐሳብ ጥራት ከማጣቱ የተነሳ ፕሮፌሰር መስፍን እንደልማዳቸው ከሥራቸው አረፍ ለማለት ለቡና ወደ ቶሞካ ጎራ ሲሉ ሌላ ሰው ጽፎ ያስቀመጠው ይመስላል፡፡ የዚህ መጽሐፍ ክፍል መበላሸት አሳዛኝ የሚኾነው፤ ፕሮፌሰር መስፍን ሊያስተላልፉ የፈለጉትን መልእክት በተገቢ እና ጠንካራ የመከራከሪያ ሐሳቦች እንዳይደገፉ በማድረጉ እና በዝባዝንኬ ዋናውን መልእክት እንዳያፍታቱ ጋሬጣ ኾኖ መገኘቱ ነው፡፡

በአካል የአፍሪካ ቀንድ ውስጥ ኢትዮጵያ የምትባል ፖለቲካዊ ግዛት ያላት አገር መኖሯን አልጠራጠርም። በዚች ግዛት ውስጥ ግን በአንድ ዐይነት ወይም ቢያንስ በተቀራራቢ ምናባዊ ማሕበረሰብ ውስጥ (Imagined Community) የሚኖሩ ዜጎች አሉ ብዬ አፌን ሞልቼ ለመናገር ግን አልደፍርም። ምናባዊ ማሕበረሰብ ስንል በአንድ ፖለቲካዊ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች ስለሚኖሩባት አገር ታሪክ ፣ ማንነት እና ፍፃሜ አንድ ዐይነትም እንኳን ባይኾን እጅግ ተቀራራቢ የኾነ ምስል መቅረጽ ሲችሉ ነው። ምናባዊት ኢትዮጵያ ተፈጥራለች የምንለው ሲያዴ፣ አበበ፣ ተስፋዪዮን፣ ጀሚላ እና አሌሮ ስለ ኢትዮጵያ አንድ ዐይነት ምስል ሲፈጠርላቸው ወይም ስለኢትዮጵያ ተቀራራቢ መግለጫ ሲሰጡን ነው።

ፖለቲካዊ ሕልውና አንድን ግዛት ከወራሪ በመከላከል እና አጠገብ ያለን አገርም ኾነ መንደር በውድም በግድም በማስገበር ይፈጠራል፣ ይሠራል። አገሮች ሁሉም የተገነቡት በዚህ ታሪካዊ እና ተፈጥሯዊ መንገድ ነው። ከምናባዊ ማሕበረሰብ የሚወለደውን መንፈሳዊውን አንድ አገር ለመገንባት ግን ረጅም፣ ውስብስብ እና አታካች የኾነውን ውስጣዊውን የፖለቲካ የባሕል ጉዞ መጓዝ ግድ ይላል። ፕሮፌሰር መስፍን አሁንም አብዛኛው ተደጋጋሚው ትኩረታቸው እና ቁጭታቸው የሚያተኩረው ከውጭ ወደ ውስጥ በኢትዮጵያ ላይ ስለሚደረግ የዳር ድንበር ጥቃት ነው።

ለፕሮፌሰር መስፍን እና መሰሎቻቸው ዐይነት የኢትዮጵያ አማኞች የኢትዮጵያን ምናባዊ እና መንፈሳዊ ሕልውና እንዲጠይቁ መጠበቅ አንድን ዲያቆን የተገለጠውን እውነት እንዲጠይቅ የመጋበዝ ያህል ይኾንብኛል። ፕሮፌሰር መስፍንን በዚህ ጉዳይ መሞገትም ኾነ ከፕሮፌሰር መስፍን ጋር በዚህ ጉዳይ መወቃቀስ ከዲያቆን ጋር ከመጨቃጨቅ ስለማይለያይ የሚበጀን ፕሮፌሰር መስፍን ስለ "ክሽፈት" የከፈቱልንን ተዋስዖ በመጠቀም ለምን አንዲት ዐይነት ምናባዊ ኢትዮጵያን ሳንፈጥር ቀረን? ለምን በዚህ የቤት ሥራ ከሸፍን? ብለን አዲስ ጥያቄ፣ አዲስ የቤት ሥራ ለራሳችን መስጠት ይሻላል።





ዳርድንበሯ ስላልተደፈረችው ኢትዮጵያ ሕልውና በማውራት፣ በመሸለል እና መፎከር ብቻ ጊዜ ከማጥፋት ስለምናባዊቷ ኢትዮጵያ ሕልውና መጨነቅ የሚገባን ጊዜ ላይ ደርሰናል። ፕሮፌሰር መስፍን በዚህ መጽሐፋቸው ያነሷቸው ጥልቅ መንፈሳዊ እና ፍልስፍናዊ ጥያቄዎችን ስናሰናነስል፣ ራሳችንን መጠየቅ ያለብን ስለአካላዊቷ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይኾን ስለመንፈሳዊቷ ኢትዮጵያም ጭምር ነው። በተለምዶው በኢትዮጵያ ተዋስዖ ስለምናባዊዋ ኢትዮጵያ ሲወራ የራሱን ምናባዊ ኢትዮጵያ ሁላችንም ላይ ይጭናል እየተባለ የሚከሰሰው የእነፕሮፌሰር መስፍን ቀኝ ዘመም መንደር ነው፡

በዚህ መጽሐፋቸው ፕሮፌሰር መስፍን በተደጋጋሚ "ወያኔ ወያኔ" እያሉ ሲጮሁ እናም ወያኔን እንደ ኢትዮጵያዊ ሳይኾን እንደ አንድ ባዕድ አካል ሲቆጥሩ ሳይ ቀረቀረኝ። እስከመቼ ነው ወያኔ ወያኔ የምንለው? እስከመቼ ነው የእነመለስን ኢትዮጵያዊነት የምንጠራጠረው? ለዚህኛው ጥያቄዬ መልስ ከመስጠቴ በፊት ግን በአእምሮዬ ሌሎች ጥያቄዎች መጡብኝ። የእነመልስ ቡድን እና ትውልድ ለአንዲት የጋራ ምናባዊ ኢትዮጵያ መፈጠር ምን አስተጽኦ አበረከተ? ይህ የህወሓት ቡድን ሥልጣን በያዘበት ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ የራሱን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ከማጋበስ እና ከማስፋፋት አልፎ ከእኛ እንደ አንዱ የሚያስቆጥርው እና ለኢትዮጵያውያን በሙሉ የሚጠቅም ምን ነገር አበረከተ? ይህን የአእምሮዬን ጥያቄ ዝም ብሎ መሻገር አቃተኝ።

የብሔር ብሔረሰቦች መብት አስከብራለው ብሎ የጮኸው ኢሕአዴግ ዛሬ ኢትዮጵያን ወደ ትልቅ የብሔሮች እስር ቤት እና የብሔሮች መናቆሪያ መድረክነት ለውጧታል። ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ለማድረግ የሚያስችሉ አጋጣሚዎችን በሙሉ እየሸሸ ኢትዮጵያን በዓለም ላይ ትልቋ የባሕር በር ዐልባ አገር አድርጓታል። መሬት ለአራሹ ብለው የዘመሩት እነ በረከት ስምዖን አያቶቻችን ለምዕተ ዓመታት በጠላት ባለቤትነት እንዳይያዝ የሞቱለትን መሬት ለዐረብ፣ለቻይና እና ለኮሪያ ነጋዴዎች እና ኮርፖሬሽኖች ረከስ ባለ ዋጋ ለአንድ ዓመት ሳይኾን ለመቶ ዓመት እየቸበቸበው ነው። ታዲያ በምን መሠረት ላይ ቆሜ ፕሮፌሰር

መስፍንን "የእነ መለስን ኢትዮጵያዊነት ተቀበሉ!" ልበል? ይህን ሁሉ የታሪክ ጉድ እየኖርኩኝ በምን ማስረጃ ላይ ተመሥርቼ ለአንዲት ምናባዊ ኢትዮጵያ አለመፈጠር ተጠያቂው የእነፕሮፌሰር መስፍን ካምፕ ብቻ ነው ልበል? ከዚህ የክሽፈት አዙሪት ማን ያወጣናል? ክሽፈቱ ዙሪያ ጥምጥም ነው። አንዱ ለራሱ የሳለው ምናባዊ ኢትዮጵያዊነት ሌላው ከሳለው ምናባዊነት ጋራ የሚለያየው በጠላትነት እስከመፈራረጅ በሚያደርስ ልዩነት የሚገለጥ ነው። በሁለት በኩል በተሳለ ቢላ ላይ የተቀመጠ ምናባዊነት።

ፕሮፌሰር መስፍን ስለክሽፈት ሲተነትኑ በመስክ በመስኩ በዘርፍ በዘርፉ መደርደር መርጠዋል። ቴክኖሎጂ ከሽፏል፤ ልማት ከሽፏል፤ በሕግ መተዳደር ከሽፏል፤ ንግድ ከሽፏል፤ ኢንዱስትሪ ከሽፏል፤ እርሻ ከሽፏል እያሉ በየዘርፉ ክሽፈትን ያትታሉ። በዘርፍ ማስቀመጥ አልበቃ ካላችሁ ይመስላል በኢትዮጵያ የከሸፉ የሚሏቸውን ተቋማት ይዘረዝራሉ። እዚህ ዝርዝር ውስጥም ራሳቸው አፈር ፈጭተው እና ጭቃ ጠፍጥፈው የፈጠሩትን ኢሰመጉን ያስቀምጣሉ። "ኢሰመጉን ወያኔ አከሸፈው ይባላል እንጂ እኛ ከሽፈን አከሸፍነው አንልም" በማለት ራሳቸውን ከዚህ የክሽፈት አዙሪት ውጭ አድርገው እንደማያዩ፤ እርሳቸው የነኩት አንዳንዱም እንደከሸፈባቸው በምሬት ይናገራሉ። ይህ የፕሮፌሰር መስፍን የክሽፈት ትርጓሜ እና የከሸፉ ዘርፎች፤ የከሸፉ ተቋማት፤ እና የከሸፉ ፕሮጀክቶች ዝርዝር የመልእክታቸው አንደኛው ክፍል ነው። በዚህ ክፍል ፕሮፌሰር ያስቀመጡት መልእክት ኢትዮጵያ ራሷ ሕልውና ከማስጠበቅ አልፋ እንደ አገር አንድም ርምጃ እንዳልተራመደች ነው። ዝርዝሩ የቀረበበት አንደኛው ምክንያት ተፈጥሯዊ ግዴታውን እየተወጣ ለረጅም ጊዜ ያለማቋረጥ እያደገ፣ እየተመነደገ፣ እየገሰገሰ ያለምንም መጨናገፍ የቀጠለ ዘርፍም ኾነ ተቋም እንደሌለን ለማስረገጥ ነው።

ይህ ምን አዲስ ነገር አለው? እነዚህን የኢትዮጵያን ክሽፈቶች መዘርዘር እኛ ራሳችን በየጊዜው እና በየአጋጣሚው ከምናወራው ክሽፈት በምን ተለየ ብሎ የሚጠይቅ ሰው ሊመጣ ይችል ይኾናል። መልእክቱ እና መልእክተኛው ሚዛን ላይ





የሚቀመጡት እንግዲህ ይኼኔ ነው። ፕሮፌሰር መስፍን በሞያም፤ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ፖለቲካ፣ ታሪክ፣ ማኅበራዊ ሕይወት እና ሚዲያ ባላቸው ተሳትፎ ለአገር አድባር ሊባሉ ከሚገባቸው ጥቂት ሰዎች መካከል አንዱ ናቸው። ኢትዮጵያን እጅግ ከመውደዳቸው የተነሳ ለማቀፍ ሲንደረደሩ ሊያንቋት ከሚዳዳቸው የቀኞች ወገን ፓትያርክም አያቶላህም ናቸውና እርሳቸው የሚናገሩትን ባንወደው እንኳ የኢትዮጵያን ፖለቲካ እከታተላለሁ የሚል ቃላቸውን ችላ ሊል አይችልም። ዕድሜያቸውን ሙሉ በአንድም በሌላም መልክ ስደትን ሳይመርጡ ከሕዝቡ ጋር እየታሰሩም፤ እየተንገላቱም፤ እየተጋፉም የኖሩ ሰው በዚህ እድሜአቸው የሚናገሩት ነገር ተስፋ የሚጭር ሳይኾን ስለ አገርም ስለ ራሳቸውም ያቀረቡት የመረረ ትችት መኾኑ ቆም ብሎ ለማየት የሚጋብዝ ነው።

*ፕሮፌሰሩ ዝም ብለው የሽምግልና ጨለምተኝነት ተጠናውቷቸው፤ አዲሱን የኢትዮጵያ እውነታም መቀበል ተስኗቸው ነው እንጂ ስለ ኢትዮጵያ እንዲህ ድፍን ያለ ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ነገር የለም የሚሉ ሊኖሩ ይችላሉ።*

ለእነዚህ ሰዎች የምላቸው አንደኛ፦ ፕሮፌሰር መስፍን በዚህ መጽሐፍ ለብዙ ሰዎች በቀላሉ ሊዋጡ የማይችሉ ሐሳቦችን በተጀቦነ መንገድ አቅርበዋቸዋል ማለት ስለ ክሽፈት ያቀረቡትን ትንታኔ እና መልእክት የግድ ሙሉ ለሙሉ ያፈርሳል ማለት አይደለም። ፕሮፌሰር መስፍን ስለእኛ መክሸፍ ያነሷቸው ትንታኔዎች ብቻቸውን የመቆም ብቃታቸው እጅግ ጠንካራ ነው። ለዚህም ነው ንጥር መልእክቱን ከአላስፈላጊ የመጽሐፉ ክፍል ፈልቅቀን ማውጣት ያስፈለገን። ሁለተኛ፦ በዋነኛነት ከላይ ፕሮፌሰር ባቀረቡት መለኪያ ያልከሸፈ መስክ በኢትዮጵያ አለ የሚል ካለ እስኪ በማስረጃ ያቅርብ? መቼም የፈረደበትን የአዲስ አበባ የፎቅ ጋጋታ እና የመንገድ ግንባታ፣ የዐባይ ግድብ እና መሰል ፕሮጀክቶችን እንደ አለመክሸፍ ማስረጃ ለማቅረብ የምትንደረደሩ ካላችሁ ይህን ጹሑፍ ማንበብ ትታችሁ ጊዜያችሁን ልማታዊ ነገር ላይ አውሉ።

ለፕሮፌሰር መስፍን ክሽፈትን ከኢትዮጵያዊነት ጋር እንዲዋሀድ ያስቻሉት ሦስቱ መሥላሴዎች (በሕግ ሊገራ ያልቻለው

ሥልጣን፣ ሃይማኖት እና ተባብሮ ያለመሥራት) ናቸው:: "በኢትዮጵያ ጉልበት ሥልጣን ነው፣ ጉልበት መብት ነው፣ ጉልበት ሕግ ነው፣ ጉልበት ሥነ ሥርዐት ነው፣ የገዢዎች መብት ያልተገደበ ነው፣ የገዢዎች ግዴታ ያልተገደበ ነው" ገጽ 194:: ይህ ያልተገደበ ጉልበት ሰዎቸ በፍርሃት እንዲኖሩ ከማድረጉም ባሻገር ዜጎች ከአእምሯቸው ያፈለቁትን ሐሳብ አዳብረው በሥራ ከመበልፀግ እና ከማደግ ሥልጣን በመቆናጠጥ ወይም ለሥልጣን በማጎብደድ መክበርን እንዲመርጡ መሬት አደላድሏል ሲሉ ያስረዳሉ

ከዚህም የተነሳ እንደፕሮፌሰር መስፍን ትንታኔ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያ ውስጥ በአእምሮ ውጤት ወይም በሥራ ለመበልጸግ ከመጣር በሥልጣን መበልፀግ የሚያዋጣ መንገድ መኾኑም ተደርሶበታል:: ምክንያቱም በሕግ ያልተገራ ሥልጣን በነገሠባት ኢትዮጵያ አንድ ሰው በአእምሮው አሰላስሎ ለፍቶ የሠራውን ማንኛውንም ነገር አንድ ባለሥልጣን በፈለገው ሰዓት ሊቀማው እንደሚችል ጠንቅቆ ያውቃል:: በኢትዮጵያ ሕግ የቆመው የአንድን ሰው የአእምሮ ወይም የጉልበት ልፋት ውጤት ባለቤትነት ሕልውና ለማስጠበቅ ስላልኾነ ለአንድ ዜጋ ሠርቶ ለማደግ ምንም የሚያነሳሳ ነገር አይታይም ይላሉ ፕሮፌሰር:: እንዲያውም ለመበልጸግ ከመጣር ይልቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድህነትን እንደጥቃት መከላከያ ተሸፋፍኖት ይቀመጣል፣ ወይም ባለሥልጣን ቢኾን ሀብት አጋብሶ ሀብቱን በሥልጣኑ ያስጠብቃል:: "በሕግ እና በሥርዐት የሚገዛ አስተዳደር ከሌለ የማኅበረሰቡ እድገት እና እና መሻሻል እንኳን ወደፊት ሊሄድ እና ባለበት ለመቆየትም ያዳግተዋል" ገጽ 23::

ፕሮፌሰር መስፍን በኢትዮጵያ ያልከሸፈ ነገር ስለአለመኖሩ የሰጡን ትንታኔ ትክክለኝነት የሚጠራጠሩ ካሉ ስለየትኛዋ ኢትዮጵያ እንደሚያወሩ እንጠይቃቸዋለን:: ነገር ግን ቀደም ሲል ስለ ምናባዊት ኢትዮጵያ ሕልውና ስንወያይ ያነሳናቸው የምናባዊ ማሕበረሰብ ግንባታ ነጥቦች አስፈላጊነት በድጋሚ የሚነሳው እንግዲህ እዚህ ጋር ነው:: አንድ ዐይነት ወይም ተቀራራቢ ምናባዊ ማሕበረሰብነት የሌለው ሕዝብ እንዴት አድርጎ አንድ





የጋራ መተዳደሪያ፣ ደንብ፣ ሕግ፣ ሥርዐት እና ተቋማት የሚወልደው አንድ ምናባዊ ማሕበረሰብ ሳንፈጥር እንዴት ወደ አንድ አቅጣጫ ማየት እንችላለን? ይህን ጥያቄ የመጀመሪያ ደረጃ (First Order) ጥያቄ ልንለው እንችላለን:

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በርካታ ብሔሮች አገር አንድን ወጥ ምናባዊ ማሕበረሰብ መፍጠር ያረጅም ዘመን ሥራ ነው:: ስለዚህ አንድን ምናባዊ ማሕበረሰብ እስክንፈጥር የሕግ የበላይነትን አስመልክቶ በርካታ ሥራዎች መሥራት ይቻላል:: አገሮች የረጅም ጊዜ ተጓዥ ናቸውና የመጀመሪያ ሥራውን እስክንጨርስ ከምንጠብቅ ከሥር ከሥር ሕግ እና ሥርዐት እየገነባን ቀስ በቀስ አንድ ምናባዊ ማሕበረሰብን ወደመገንባት መሄድ እንችላለን የሚሉም ይኖራሉ:: የእነዚህ ሰዎች ትኩረት የመጀመሪያ ደረጃ ጥያቄዎችን በመመለስ ላይ ሳይኾን ሁለተኛ ደረጃ (Second Order) ጥያቄዎችን በመመለስ ላይ ነው::ይህ የቅደም ተከተል ጥያቄ መኖሩን ከማሳየት አልፎ 'ይህ ይቅደም፣ ይህ ይከተል' ወደሚለው ውይይት በጥልቀት ብገባ የጽሑፉን ትኩረት ያዛባብኛል::

ቢያንስ ከአብዮቱ ጊዜ አንስቶ በኢትዮጵያ ሥልጣንን ለመገደብ የተሻለው አማራጭ የመጀመሪያውን ጥያቄ መመለስ (እንዴት ምናባዊት ኢትዮጵያን መገንባት)፣ አይደለም የሁለተኛውን ደረጃ ጥያቄ መመለስ (ሕግ ማውጣት ተቋማትን መገንባት) ነው በሚል በርካታ ሙከራዎች ተደርገዋል:: ፕሮፌሰር መስፍን በሚያነሷቸው መለኪያዎች ከተወያየን ግን በኢትዮጵያ በሁለቱም መንገድ ሥልጣንን ለመገደብ የተደረጉት ሙከራዎች ከሽፈዋል:: ስለዚህ ጥያቄው የቅደም ተከተል መኾኑ ይቀራል:: ተጨማሪ የክሽፈት ሂደት:

ፕሮፌሰር መስፍን ለኢትዮጵያ የክሽፈት ማንነት ምንጭ የሚሉት ሌላው ነገር ሃይማኖት ነው:: ፕሮፌሰር በሃይማኖት ላይ የሚያቀርቡት ትችት በግልጽ የተነጣጠረው ሃይማኖት ለአስተሳሰባችን ከሚጫወተው የእውነት ምንጭነት (Epistemic Role) ጋራ በተያያዘ መልኩ ነው:: ፕሮፌሰር ሁለት የእውነት ምንጮች እንዳሉ በዚህ ትንታኔያቸው ያስቀምጣሉ:: አንደኛው

የእውነት መሠረት እምነት ነው። ከእምነት የሚመነጨውን እውነት ፕሮፌሰር "የተገለጠ እውነት" ሲሉ ያስቀምጡታል። ይህ እውነት በባሕርይው አይጠየቅም፣ አይገረሰስም።

እንደፕሮፌሰር ሁለተኛው የእውነት ምንጭ እውቀት ነው። ከእውቀት የሚመነጭ እውነት ግን ለፈተና፣ ለጥያቄ እና ለትችት የተጋለጠ ነው። እንዲያውም ከእውቀት የሚገኝ እውነት መለኪያው ተጠይቆ የተገኘ እና የተፈተነ መኾኑ ነው። ከመገለጥ የተገኘ እውነትነትን አዳጋችነት ሲያስቀምጡ "በአንድ ጉዳይ ላይ በአንድ ጊዜ ሁለት በፀጋ የተገለጡ ተቃራኒ እውነቶች ሲኖሩ ቅራኔው የሚፈታው እንዴት ነው?" ገጽ 196 ሥልጣንን መግታት ያልቻልንበት አንዱ ምክንያትም ይላሉ ፕሮፌሰር "ሥልጣን በፀጋ ከተገለጠ እውነት ጋር በመያያዙ ነው።" ከዚህ ሃይማኖታዊ እውነታ የወለድነውን ማኅበራዊ ውል (Social Contract) ፕሮፌሰር "ገዢዎች ረግጠው ለመግዛት ተገዢዎችም በበኩላቸው የተገለጠ እውነት እየተጠቀሰላቸው ለመገዛት የተስማሙበት .." በማለት ይገልሹታል

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከተቀመጡት ዕንቁዎች ውስጥ ለእኔ ትልቁ ዕንቁ ይህ ፕሮፌሰር ስለተገለጠ እውነት የሰነዘሩት ትችት ነው። ፕሮፌሰር ፍልስፍናን ማንበብ ብቻ ሳይኾን ከሚኖሩበት ማሕበረሰብ እና እውነታ ጋር እንደሚያጋቡት ትልቅ ማስረጃ ነው። በአገራችን ፍልስፍናን ማንበብ እንደጀመሩ ሃይማኖት ላይ መሳለቅ ፋሽን ነው። እነዚህ ጀማሪ የፍልስፍና አንባቢዎች ስለሃይማኖት እና ኢትዮጵያ ሲያስቡ ብዙ ጊዜያቸውን የሚያጠፉት በዓላት እያበዛ ሥራ አስፈታን፣ ታታሪ እንዳንኾን አደረገን የሚል አርቲ ቡርቲ መከራከሪያ በማቅረብ ነው።

እንደ ፕሮፌሰር መስፍን አገላለጽ ሃይማኖት ለክሽፈት መበራከት ዐይነተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል። እርሳቸው ይህን ከሥልጣን አለመገደብ ጋራ አሰናስለው በሰፊው ትንታኔ ሰጥተውበታል። ነገር ግን ይህን ጉዳይ ከእውነት ምንጭነት ጋራ በማገናኘት ሃይማኖት የመናገር ነጻነትን እንዴት ዋጋ አሳጥቶት እንደኖረ መተንተን እንችላለን። ለምሳሌ ገጣሚ እና ደራሲ በእውቀቱ ስዩም አቡነ ተክለሃይማኖትን ተችቷል ተብሎ በቡጢ





የተመታ ጊዜ አሳፋሪ በሚባል መልኩ ትንሽ ትልቁ ለበእውቀቱ እና ሐሳብን ለመግለጽ ነጻነት ከመቆም ይልቅ "ስቀለው!"፣ "ስቀለው!"፣ "ስቀለው!" ሲል ዐይተናል። እንዴት ነው ይህ ማሕበረሰብ የተለያዩ እውነታዎችን በአንድ እና ተመሳሳይ ጊዜ ማስተናገድ የሚችለው? እንዴት ነው ሳይንስ በዚህ ወደ በደነቆረ ማሕበረስብ ውስጥ የሚያድገው? ዛሬ አቡነ ተክለሃይማኖት የማይነኩ ከኾነ፣ ነገ ደግሞ በሌላው አገር እንደሰማነው ነብዩ መሐመድን ተናገራችኹ ተብለን ፈጠዋ ሲታወጅብን ነው ማለት ነው? የተረጋገጠ እውነት ሳይኾን ሃይማኖታዊ እውነት በሚገነባበት ማሕበረስብ እንዴት ነው አንድ ዐይነት ምናባዊ ማሕበረስብ የምንገነባው? ማን የማን ሃይማኖት በገነባው ምናባዊ ማሕበረሰብ ጥላ ስር ሲኖር?

ፕሮፌሰር ለኢትዮጵያ የክሽፈት ባህል መንስዔነት የሚከሱት ሌላኛው ነገር አብሮ ያለመሥራት እና ያለመተባበር ዝንባሌያችንን ነው። እንደ ፕሮፌሰር ዕይታ ትብብራችን በሙሉ ከመቃብር እና ከተዝካር ያለፈ ትልቅ ነገር ሲወልድ፣ ሲያሳድግ እና ለማዕረግ ሲየበቃ አልቻለም። ፕሮፌሰር ለክሽፈት ምክንያትነት ካቀረቧቸው ሦስት ምክንያቶች ስለ አለመተባበር ያቀረቡት መከራከሪያ በእጅጉ አናሳ ነው። ስለ እውነት፣ ስላልተገራ ሥልጣን ያብራሩትን ያህል ስለተባብሮ አለመሥራትም ብዙ ሊሉ ይችሉ ነበር።

ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ እጅግ በጨነቀው የመጨረሻው ሰዓት "ኤሎሄ ኤሎሄ ላማሰብቅታኒ" ያለው ሲሰብክበት በነበረው የእብራይስጥ ቋንቋ ሳይኾን አፉን ፈትቶበታል ተብሎ በሚገመተው የአረማይክ ቋንቋ ነበር። ኢየሱስ ይህን መልዕክት ለመናገር ለምን የአረማይክ ቋንቋን እንደተጠቀመ በርካታ ሃልዮቶች አሉ። እኔ የሚስማማኝ ኢየሱስ አፉን በፈታበት ቋንቋ ይህን ሰቆቃ ያቃስተው በሕይወታችን የመጨረሻ ወቅት ሰቆቃ ሲገጥመን የምናቃስተው በተማርነው ቋንቋ ሳይኾን አፋችንን በፈታንበት ቋንቋ ስለኾነ ነው የሚለውን የሥነልቦና ምሁራን ሃልዮት ነው።

ለፕሮፌሰር መስፍን ትውልድ የኢጣልያ ወረራ እጅግ ዘግናኝ እና ወሳኝ የሰቆቃ (Trauma) ምንጭ እንደኾነ መጽሐፋቸውን በማየት መረዳት ይቻላል፡፡ በኢጣልያ ወረራ ወቅት አርበኞች ቢኖሩንም የነበረን የባንዳ ብዛት እና በመጨረሻም አገር ነጻ ስትወጣ አርበኛ ሳይኾን ባንዳ ሲያሸንፍ መመልከት በወቅቱ ልጆች እና ወጣት ለነበሩት ለእነ ፕሮፌሰር መስፍን የዕድሜ ልክ ጠባሳ ትቶ አልፏል፡፡ ፕሮፌሰር በዕድሜያቸው መጨረሻ በሰቆቃ ላይ ሰቆቃ እያስተዋሉ ይኼው በመጨረሻ ላይ አፋቸውን በፈቱበት የክህደት ትዕይንት ኢትዮጵያ ተውጣ እያዩ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ተባብሮ አለመሥራት (Collective Action) እጅግ ያቃተን ለምንድን ነው? በተለይ በተለይ ኢትዮጵያዊነት/ኢትዮጵያ የሚሉት ነገሮች አስተባብረው ከአንድ ቦታ ለማድረስ ለምን ሰነፉ? ሐበሻ ለብሔሩ ሲኾን መንግሥት ይጥላል (ትግሬ፣ ኤርትራ) ለሃይማኖት ሲኾን አንድ ዓመት ሙሉ በሰላማዊ መንገድ ይታገላል፡፡ ይኼው ሙስሊሞች ሰላማዊ ትግል ከጀመሩ አንድ ድፍን ዓመት ኾናቸው፡፡ ስለ ኢትዮጵያ ሲባል ለምን ሐበሻ ልቡ ይፈሳል? ይህ አብሮ ያለመሥራት ስንፍና እና ታካችነት ምንጩ የት ጋር ነው?

## የክሽፈት ተዋስዖ

ፕሮፌሰር መስፍን በዚህ መጽሐፋቸው አዲስ የክሽፈት ተዋስዖ ፈልፍለዋል እላለኹ፡፡ አዲስ ስል ግን ከምንም የተነሳ ምንም ከሌለበት ውስጥ አዲስ የተወለደ (Ex nihilo) የሚባለውን ዐይነት አፈጣጠር አይደለም፡፡ ለዚህም ነው ፈጥረዋል ከሚለው ቃል ይልቅ 'ፈልፍለዋል' የሚለውን የመረጥኹት፡፡ መፈልፈል ከእንጨት፣ ድንጋይ ወይም መሰል ተጨባጭ ነገር ውስጥ የራስ የኾነን ፈጠራ በመጨማመር አዲስ ነገርን ፈልቅቆ ማውጣትን ያመለክታል፡፡

በአንድም ኾነ በሌላም መልኩ ስለመክሸፍ የኢትዮጵያ ምሁራን አውርተዋል፡፡ ለምሳሌ የተማሪዎች አብዮት ከሽፏል





አልከሸፈም? (ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ) ኢሕአዴግ የመራው የሽግግር መንግሥት ከሽፏል አልከሸፈም? (ሌንጮ ለታ) አነግ ከሽፏል አልከሸፈም? (ጃዋር መሐመድ) እነዚህ ምሁራን በፍልስፍና፣ ፖለቲካ እና ታሪክ በኩል መክሸፍ ሊዳስሱት የሞከሩት ጥያቄ ነው፡፡
ከመክሸፍ ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ የሚነሳው ሌላው ጥያቄ ኢትዮጵያ የተለያዩ የጥናት ተቋማት የሚያወጧቸውን የከሸፉ አገራት (Failed States) ዝርዝር ማሞቅ ከጀመረች ሰንበታለች፡፡ ኢትዮጵያ በእነዚህ የከሸፉ አገራት ዝርዝር መካተቷ አሳማኝ የማይሆንባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ምንኛ ተዳክሟል፣ተልፈስፍሷል ቢባል በፈለገው ሰዓት የፈለገው የግዛቱ ክልል ውስጥ ያለማቋረጥ እንቀጥቅጦ ግብር ይሰበስባል፡፡ የተለያዩ አቅርቦቶችን ለዜጎች ያከፋፍላል ለምሳሌ መንገድ ይሰራል፣ ሰዎችን በሰላም አስወጥቶ በሰላም ያስገባል፣ ለሰራተኛ ደሞዝ ይከፍለል፡፡ ይህን አይነት ጠንካራ መንግስት መቼም መንግስት የሚባል ከሌለበት ከሶማሊያ ወይንም የመንግስት ሰራተኛ ደሞዝ ካየ አምስት አመት ከተቆጠረባት ኮንጎ ጋር ማወዳደር አዳጋች ነው፡፡ እንደውም ይህ የመንግስት ጥንካሬ (Strong State) ባሕሪይ የኢትዮጵያን መንግስት ከአፍሪካ በርካታ መንግስታት ጋር ሲነጻጸር አልከሸፈም ለማለት ሊጋብዘን ይችላል፡

ፕሮፌሰር መስፍን ስለክሽፈት የሰጡት ሁለተኛ ትርጓሜ እንደሚያስታውሰን መክሸፍ ማለት የተነሱበትን ግብ አለመምታት ብቻ ሳይሆን አለማደግ ፣አለመሻሻል ፣ ባሉበት ፣በጀመሩበት መቆም ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ጥንካሬ የጀመረው ዛሬ አይደለም፡፡ ከአፈጣጠሩ የኢትዮጵያ መንግስት እጅግ ጨካኝ እና መራራ መንግስት ነው፡፡ እስቲ ግብር የሚለውን ቃል ትርጉም አስተውሉ፡፡ ማንበርከክን ፣ማሰቃየትን፣ አገር ማስፋፋትን፣ ገቢ ከመሰብሰብ ጋር አዋህዶ የያዘ አስገራሚ ፖለቲካዊ ቃል ነው፡፡ በኢትዮጵያ መሸፈት የሚጀመረውም አልገብርም ወይንም ግብሩ በዛብኝ ከሚል እምቢተኝነት ነው፡፡ ይህ የእምቢተኝነት አዙሪት ግን የሚጠናቀቀው የግብር ስርአቱን በማሻሻል ወይንም በማላላት ሳይሆን ከቀደመው ስርዓት እስከፊ በሆነ መልኩ አስገባሪ በመሆን

ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት አሁንም ጠንካራ አስገባሪ ነው ነገር ግን መንግስት የመሆን ጽንሰ ሀሳብ አስገባሪ ብቻ ከመሆን ከሰፋ ስንት ዘመኑ?

ፕሮፌሰር መስፍን ስለክሽፈት እና ኢትዮጵያ የሚያነሱትን ጥያቄ በአቀራረብ ልዩ ያደርገዋል የምልበት ሌላው ምክንያት የመክሸፍን ክስተት ከአንድ ታሪካዊ አጋጣሚ ወይም ፕሮጀክት አውጥተው ከማንነት ጋር በማያያዛቸው ነው፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን ስለ ክሽፈት እና ኢትዮጵያዊነት ያላቸው ትንታኔ በኢትዮጵያ ታሪክ ክሽፈት ድግግሞሽ መኾኑን በማሳየት ከጀመረ በኋላ ክሽፈት ባህል ነው ወደሚል ድምዳሜ ይሻገራል፡፡ ይህ ድምዳሜያቸው ክሽፈትን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በአንድ ወቅት ወይም በተደጋጋሚ ከሚታይ አጋጣሚ ወደ አንዱ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ያሸጋግረዋል፡

ይህ ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ ሐሳቦች፣ ዕቅዶች፣ ተቋማት የሚከሽፉት አመቺ ኹኔታዎች ስላልተፈጠሩላቸው ብቻ ሳይኾን መክሸፍ ኢትዮጵያዊነትን ከኬንያዊነት እንዲሁም ከጃፓናዊነት ከሚለዩት ልዩ ባሕርያት አንዱ ስለኾነ ነው ማለት ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ ከኾንክ/ከኾንሽ መክሸፍ ባህልህ/ባህልሽ ነው፡፡ በአጭሩ ኢትዮጵያዊ መክሸፉን ነብር ዥንጉርጉርነቱን አይተውም፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያውያን በግልም ኾነ በጋራ የምንሠራው ነገር በሙሉ ገና ሳንተገብረው ክሽፈትን ፀንሷል፡፡ ይህ የክሽፈት ፅንስ የተቀመጠው በማንነታችን ውስጥ ነውና እንደፕሮፌሰር አባባል ከአገር ስንሰደድም ይዘነው እንጓዛለን፤ ስደታችንም ገና ከቦሌ ሳንደርስ ይከሽፋል፡፡

የፕሮፌሰር መስፍንን መልእክት በአትኩሮት እንደከታተል ያደረገኝ ሌላኛው ነገር ስለታሪክ ያላቸው ምሬት ከተለምዶው የቀኞች መንደር ምንጭ ብቻ የተቀዳ አለመኾኑ ነው፡፡ ስለኢትዮጵያ ታሪክ እንዲኖረን የሚሹት ትውስታ(Memory) አሁንም ልክ እንደ ርዕዮተ ዓለማዊ መንደራቸው በጋራ ጭቆና እና የጋራ ጋሬጣ ላይ ብቻ መኾኑ አልቀረም፡፡ ነገር ግን ከታሪክ ትንታኔ ብቻ ወጥተው ወደ ታሪክ ፍልስፍና (Philosophy of History) ሲጓዙ ስለኢትዮጵያዊነት የሚያቀርቧቸው የክሽፈት





ትችቶች ከርዕዮተ ዓለም እስረኝነታቸው ፈታ ለማለት ሲታገሉ ይታያል፡፡ በርዕዮተ ዓለም ብቻ የታሠረ የኢትዮጵያ የቀኝ መንደርተኛ ኢትዮጵያን/ኢትዮጵያዊነትን ከሽፋለች ለማለት አንጀት የለውም፡፡ቀኞች በተለምዶ ስለክሽፈት ሲያወሩ እነርሱ አገር ስላልገዙ የእነርሱ ፕሮጀክት ስለከሸፈ አገሪቷ የከሸፈች ይመስላል፡፡ የፕሮፌሰር የክሽፈት ትንታኔ ከቀኝ መንደር የተለቀሙ ቅመሞች የበዙበት ቢኾንም መልእክቱ እና የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ፈጽሞ ችላ ልንላቸው የሚገቡ አይደሉም፡፡

አንድ ተዋስዖ የሚጀምረው ተዋስዖው ራሱ ሊያወያየው የሚፈልገው ጥያቄ ተገቢ ነው አይደለም? ጥያቄው አለ ወይስ የለም? የሚሉትን ጥያቄዎች በመዳሰስ ነው፡፡ የፕሮፌሰርን መጽሐፍ በብዙ የመጻሕፍት መለኪያዎች የከሸፈ ልንለው ብንችልም መልዕክቱን ከመጽሐፉ ጋር አሽቀንጥረን ከጣልነው ግን እኛ ከመጽሐፉም ከፕሮፌሰር መስፍንም ይልቅ የከሸፍን እንኾናለን፡፡ ይልቁኑ ፕሮፌሰር መስፍን የከፈቱልንን የክሽፈት ጥያቄ ቀዳዳ ወደ ትልቅ በርነት በርግደን በመግባት ራሳችንን መበርበር እንጀምር፡፡ ስኬት ሩቅ ነች፤

በመንገዷ የሚገናኛትም/የሚደርስባትም እንደከሸፈ በማመን ጉዞውን የጀመረው ብቻ ነው፡፡

የፕሮፌሰርን መጽሐፍ ሳነበው ከስድሳ ዓመታት በላይ ኢትዮጵያን አሻሽላለኹ፤ ለሕዝቤ አገለግላለኹ ብላ የምትታገለው ነፍሳቸው በራሷ ጉዞ የገጠማት ስንጥቅ ታየኝ፡ከዚህ የነፍሳቸው ስንጥቅ የሚወጣውን መልዕክት መዓዛ ደግሞ በደንብ አውቀዋለኹ፡፡ "በእኔ ዕድሜ ያደኩበት ሰፈር ስም፤ የተማርኹበት ተማሪ ቤት ስም፤ ያስተማርኹበት ተማሪ ቤት ስም፤ የሠራኹበት መሥሪያ ቤት ስም ተለውጧል፡፡ ስለዚህ እኔ የሌለ ሰፈር አድጌ፤ የሌለ ተማሪ ቤት ተምሬ፤ የሌለ ተማሪ ቤት አስተምሬ፤ የሌለ መሥሪያ ቤት ሰርቼ፤ የሌለ ዩኒቨርስቲ አስተምሬ ... እኔ በጡረታ መኖሬ ያስገርማል! ከሽፎ የከሸፈ ኑሮ መኖር እንበለው!" ፕሮፌሰር መስፍን መልካሙን ገድል ተጋድያለኹ, ማለት በሚገባቸው የሕይወት ዘመናቸው ላይ 'ከጓቱ! ሁሉም ነገር ከንቱ!' የሚሉ

አይመስልምን? ነፍስ ስትሰነጠቅ እውነት እውነቱን እንዲህ ታናግራለች።

**************************************************

ትችት አምስት በከፍሉ ሁሴን

ነብር ዥንጉርጉርነቱን ግራ-ዘመም ኢትዮጵያዊ

ክሽፈቱን

ታምራት ነገራ በፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም "መክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ" መጽሐፍ ላይ የሰጠውን አስተያየት ካነበብኩት በኋላ የመጣብኝ ሃሳብ ሰውዬው የሚለውን ያውቀዋልን የሚል ነው። እንደምፀት ሆኖ አሁን በማላስታውሰው ምክንያት ግን በወቅቱ በወደድኩለት አንድ የፌስቡክ አስተያዬቱ ብዙም በአንባቢነትና ዓለማቀፍ ነገሮችን በመተንተን ችሎታው የማላማው ይልቁንም የእሱን ዓይነት ሃይማኖት ያላቸውን ሰዎች "የአዲስ ኪዳን በግ ቅዱስ ካህን፤የፅድቅ ንጉሥ የዓለም መድኅን" እያልኩ የምመሰጥበት ሌላ ጓደኛዬ በዚያው እኔ የታምራትን አስተያዬት "ላይክ" ማድረግ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የፌስቡክ ባልንጀሮቼ ባቃመስኩበት ወቅት "ይህ ታምራት የሚለውን ያውቀዋልን?" ሲል የጠየቀውን አስታወሰኝ። ምናልባት ጌታን በተቀበለና ባልተቀበለ መካከል ያለ ልዩነት ይሆን?ጌታን እስከዛሬ ባልቀበልም (ጌታ ነው ከሚሉትም ጋር ጌታ አይደለም ብዬ ጠብ እንደማላበቅልም ልብ ይባልልኝ) ባንዳች ምክንያት ወልይ ሆኜ ነው መሰለኝ ታምራት "ነብር ዥንጉርጉርነቱን፤ ኢትዮጵያዊ ክሽፈቱን" በሚል ርዕስ በሰጠው አስተያየት ልክ እንደዳግም ልደቱ ክርስቲያን ወዳጄ እኔም በተራዬ "የሚለውን ያውቀዋልን?" እንድል አስገድዶኛል። ታምራት የፕሮፌሰር መስፍን "መክሸፍ እንደኢትዮጲያ ታሪክ" ከመውጣቱ በፊት "The Ethiopian mind" በሚል ሲጽፍ እንዳሰበ ከነገረን በኋላ የፕሮፌሰርን መጽሐፍ ሲያነብ አንድ ላይ አጠቃሎ አስተያየቱን እንደሚያቀርብ አሳወቀን፤ በዚያው በፌስቡክ ላይ።አከታትሎም "አርታኢዎቹ" ማስረሻ ማሞ እና ዳኝነት-- እንዳሹበት አሳወቀን። ከጥቂት ቀናት በኋላም





አስተያየቱን በአዲስ ነገር የፌስቡክ ገጽ ላይ ለበደው። የእኔም በታምራት አስተያየት እና አጻጻፍ ላይ መደናገር ከዚህ ይጀምራል።

ፕሮፌሰርን ጽሑፋቸውን ወደአንባቢ ከማድረሳቸው በፊት "ለአንድ ሁለት ዙር" ትችት ለአርታኢ የመስጠት ትሕትና የላቸውም የሚለው ታምራት የእሱን ጽሑፍ ሳነብ ከአርታኢ ምንም የተጠቀመ አልመሰለኝም። ብዙ ነው ባይባልም እንኳ እሱ ፕሮፌሰር መስፍን ለአርታኢ አይሰጡም ብሎ ከተቸበት አኳያ ሲታይ ቀላል የማይባሉ የፊደል ግድፈቶች በጽሑፉ ላይ እዚህም እዚያም ይታያሉ። ለምሳሌ በአንቀጽ 3 ላይ "መናጡ እንደቀረልኝ" ሲል ፊልጎ "እየደቀረልኝ" ይላል።እንዲሁም ፕሮፌሰርን "ኢትዮጵያን ከመውደዳቸው የተነሳ ለማቀፍ ሲንደረደሩ ሲያንቋት ከሚዳዳቸው የቀኞች ወገን "ፓትያርክም" እያለ ይገድፋል። እንዴት በአርታኢ የሚያምን እና አርታኢን የተጠቀመ ጸሐፊ ጽሑፍ ውስጥ እንዲህ ያለ ግድፈት ሊኖር እንደቻለ አልገባኝም።ከሁሉም በላይ ታምራት በፕሮፌሰር መስፍን መጽሐፍ በተነሱት ቁምነገሮች መመሰጡን እየነገረን 238 ገጽ ከያዘው የፕሮፌሰር መስፍን መጽሐፍ ውስጥ ቁምነገር ያገኘው እና እንዲጽፍበት የጎነተለው በ46 ገጾች ውስጥ ብቻ ያሉት "ቁምነገሮች" እንደሆኑ ይነግረናል።

እንደታምራትም ባይሆን በትንሺ የአንባቢነት ዘመኔ ከያዘው ዳጎስ ያለ ገጽ ውስጥ ከ 80 ከመቶው በላይ ጅል ከሆነ ሃያ ፐርሰንቱ "ቁምነገር" ጋር ለመድረስ ተካልቦ በሚያካልበው የዛሬ ጊዜ ላይ ትዕግስት እንደማይኖር ጠንቅቄ ተረድቻለሁ። እና ታምራት ከሰማንያ ፐርሰንት በላይ በ"አላስፈላጊ ሐሳቦች" እና "አርቲ ቡርቲ" ተጥለቅልቋል የሚለው መጽሐፍ ላይ እንዴት ጊዜውን ወስዶ "ትችት" እስከመጻፍ እንደተጎነተለ አልገባኝም። አርታኢዎቹ በዚህ በኩል እንዲህ ያለ ሞጋች ጥያቄ ቢመጣብህ እንዴት ትከላከለዋለህ ሳይሉት ቀሩ ወይስ ያሉትን ሳይሰማቸው ቀረ? ወይስ ደግሞ "ዴሞክራት" አርታኢ የቋንቋ ግድፈት ከማሳደድ በቀር እንዲህ ያለ ጉዳይ ውስጥ አይገባም? ቋንቋን በማረምም ሆነ ሃሳብን በሚቿራት በኩል ለታምራት ያልጠቀሙ

አርታኢዎች ለፕሮፌሰር መስፍን ምን ይፈይዳሉ? የ"ቀኝ-ዘመም" ፖለቲካ እንዲህ ከሆነ በደርግ ዘመን ነፍስ እንደማወቁ ኢሕአፓ የሚባለው ቡድን የእሱን አላማ የሚጠይቁትንና የሚቃወሙትን በተለይም መኢሶን የተባለውን የባላንጣውን ቡድን "ቀኝ መንገደኛ" እያለ ስም በማጥፋት ብቻ ሳይመለስ በጥይትም እንካ ይቀመስላችሁ ይል እንደነበር አስታውሳለሁ። በንባብ ላይ ንባብ እየጨመርኩ እንዳቅሚቲ ለመንቃት በማደርገውም ጥረት በውጪው ዓለም ፖለቲካም የ"ቀኝ" የ"ግራ" የሚባል ፍረጃ እንዳለ ተረዳሁ። ያም ሆኖ በግሌ ገና ሳየው ጠረኑ ልክ (Just ) የሆነ እና ልክ ያልሆነን (Unjust ) ፖለቲካን የማፈነፍንበት ግን ስም ያልሰጠሁት የራሴን መስፈርት ስለቀየስኩ የቱ የ"ቀኝ" የቱ የ"ግራ" በሚለው እሰጥ አገባ ውስጥ ጊዜዬን አባክኜ አላውቅም። ሆኖም ታምራት የፕሮፌሰር መስፍንን መጽሐፍ "ባዘለው መልካም መልዕክት ከመሳብ ይልቅ" ከ"ቀኝ ዘመም ፖለቲካ ጠላ ጋር ተደባልቆ" ስለቀረበ በ"ጠረኑ ብቻ ብዙ ሰው ሊገፈተር ይችላል" የሚል የተምታታ ነገር ስላቀረበ የ"ቀኝ" የ"ግራ" የሚሉት ፖለቲካ ፈሊጥ ከየት እንደመጣ እና ማን በቀኝ ማን በግራ እንደሚፈረጅ ማወቂያው ጊዜ አሁን ነው ብዬ ተነሳሁ። እናም ኮሌጅ መበጠስ ሳያስፈልገኝ እድሜ ለዊኪፔዲያ ፈሊጡ ከፈረንሳይ አብዮት የመጣ መሆኑን አጫወተኝ። እጅግ የሚገርመው እንደዊኪፔዲያ ትንተና ከሆነ የፕሮፌሰር አመለካከትም ሆነ የፖለቲካ አቋም የግራ የሚባል እንጂ ከቀኝ ዘመም የሚሰለፍ አይደለም። ፕሮፌሰሩ ያልተገራ ሥልጣንን አደብ እንዲገዛ እና እንዲገራ እውነትን ለሥልጣን እየነገሩ (speak truth to power እንዲል ፈረንጅ) በሦስት አገዛዝ ዕድሜ ልካቸውን እንዳልባጁ በጥራዝ ነጠቅነትና በጀሌነት ራሱን "ግራ ዘመም" አድርጎ ሲግበሰበስ የነበረው እና የኢትዮጵያን ሕዝብ በ"መሬት ለአራሹ" እና የ"ብሔር ብሔረሰቦች የራስን እድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል መብት" ባዶ መፈክር ከግለሰብ ጉልተኞች በሰፊው ሕዝብ ስም ለአገዛዝ ጢሰኝነት አሳልፎ የሰጠውና ለአደገኛ የመከፋፈል የጎሣ ፖለቲካ የዳረገው ክፍል እስከዛሬ ፕሮፌሰር መስፍንን የ"ቀኝ ዘመም ፖለቲካ ጠላ ጠማቂ" እና አከፋፋይ ያደርጋቸዋል። የእዚህ አንድምታ





ፕሮፌሰሩን ወግ አጥባቂ እንዲያም ሲል አድሃሪ አድርጎ በመሳል ራስን ተራማጅ እና የ"ላብ አደር/ወዛደር፤አርሶ አደር፤ጭቁን ብሔር ብሔረሰብ እና የሰፊው ሕዝብ/ሕዝቦች" ተቋርቋሪ አድርጎ ለማቅረብ ነው። ይህንን ክፍል ነው ታምራት "ብዙው ሰው" ሲል ከሳለው በኋላ በፕሮፌሰር መስፍን የ"ቀኝ ዘመም ፖለቲካ ጠላ ጠረን" ይገፈተራል የሚለን። በገዛ ራሳቸው አእምሯቸውን ከ1969 ዓ.ም በኋላ እንዳያድግ አድርገው የዘጉትን ግለሰቦች ፕሮፌሰር ምን ማድረግ ይችላሉ? የቀኝ ዘመም ፖለቲካ እንደፕሮፌሰር ከሆነ እጅግ አድርጎ የሚስብ እንጂ የሚገፋተር አይደለም። ታምራት በሚኖርበት አሜሪካ ሁለት የታወቁ አንዱ አሁንም በሕይወት ያለ አንዱ ከሶስት አመት በፊት የሞተ ስመጥሩ የማህበረሰብ፣ የፖለቲካና የታሪክ ተንታኞች ይገኛሉ። በሕይወት ያለው ኖም ቾምስኪ ሲሆን ሟቹ ደግሞ ሆዋርድ ዚን ይባላል። ሁለቱም በቀይ ህንዶች እና በጥቁር አሜሪካኖች ላይ የተፈጸመውን ግፍ እያነሱ እንዲሁም የአሜሪካንን የሌሎችን አገሮች የመቆጣጠር (Hegemonic) አባዜ ያለውን የውጭ ፖሊሲውን የሞገቱ ሲሆን አንድም ጊዜ ግን በአሜሪካ ግፍ የተፈጸመባቸውን የተለያየ ዝርያ ያላቸውን አሜሪካኖች በዘር አንጻር የዘር "ነጻ አውጪ ፖለቲካ" እንዲያቀነቅኑ እንደእኛ "ግራ ዘመም" የብሔር ብሔረሰብ ተቋርቋሪዎች አልመከሩም። እንደእሱ ያለው አመለካከት ከኢትዮጵያ በኋላ በተፈጠረችው እና በራሱ የታምራት ቋንቋ "ተቀራራቢ ምናባዊ" አሜሪካንን ለመፍጠር በተሳካላት አገር አገርን እንደመክዳት ይቆጠራል ሃሳቡን ማንሳት እንኳ ባይከለከልም። በአጠቃላይ የፖለቲካ አመለካከታቸውም ሆነ ዕድሜያቸው ከፕሮፌሰር መስፍን ብዙም የማይራራቁት እነዚህ አሜሪካኖች የሚፈረጁት በግራ ፖለቲከኛነት እንጂ በ"ቀኝ ዘመም" ፖለቲካ ጠላ ጠማቂነት አይደለም። የቀኝ እና የግራው ፍረጃ እንዲህ ግልጽ ከሆነ ለምን ታምራት ሊያጨናብረን ፈለገ? ሳያውቀው የእኛዎቹ የ"ግራ ዘመም" የብሔር ብሔረሰብ ተቋርቋሪ "ፖለቲከኞች" ፕሮፖጋንዳ ሰለባ ይሆን? ጥያቄውን የመመለስ ያለመመለስ መብቱ የታምራት ሆኖ ሳለ ይህን ጽሑፉን ከአድናቂዎችም በላይ አምላኪዎችንም ያፈራችው የአዲስ ነገር ፌስቡክ ገጽ ላይ

ስለለበደው አስተያየቱ እንደወንጌል እንዳይወሰድ ሌላውን ገጽታ ማሳያት ግዴታዬ ሆኖ ተሰምቶኛል። እናም ፕሮፌሰር መስፍንን ፈረንጅ (whispering campaign) በሚለው የረቀቀ ስልት እንዴት እና ለምን ለሦቱም አገዛዝ ቅርብ የነበሩ የተለያዩ ግለሰቦች ስማቸውን ለማጥፋት እና ሥራቸውን ለማቃለል እንደተነሳሱ ሳይ። ታምራት ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ነው ለማለት ሳይሆን በእነሱ ተጨናብሮ ሊያጨናብር ተነስቷል ግን እላለሁ። ፕሮፌሰር መስፍንን መጀመሪያ በበጎ ከማያነሷቸው ሰዎች ውስጥ የዕድሜ እኩያቸው ከሆኑትና የሙያ "አቻቸው" ከሆኑት ውስጥ እንደሚገኙበት በተለያየ አጋጣሚ ለመታዘብ ችያለሁ። እነዚህ ሰዎች እንደእሳቸው ባለዲግሪ ቢሆኑም ኃይሉ ገ/ዮሐንስ (ገሞራው) "አይተኙበት ጀንዲ ዲግሪማ ነበረን በዓይነት በብዛት" የሚላቸው ዓይነት ሰነፎች ሲሆኑ በምሁርነታቸው እያነበቡ እና እየተመራመሩ ከማደግ ይልቅ ለዘውዱ ሥርዓት እጅ እየነሱና እየተሞዳሞዱ ማደግን የኑሮ ዘዴ አድርገው የያዙና ለልጆቻቸውም ሲመክሩ የነበሩ ናቸው። የመስፍን ፍጹም በራስ መተመማን ሁልጊዜ የእነዚህን ሰዎች ድኩማንነት የሚያስታውስ ስለሆነ በቅናት መንፈስ መስፍንን ማብጠልጠል አንዱ መላ ነበር። መስፍንን እና እንደእሳቸው የዘውዱን ሥርዓት የአካዳሚክ ነፃነታቸውን ተጠቅመው የሚተቹትን ለማግለል ሲባል በአክሊሉ ካቢኔ ለመስፍን የግምቢ አውራጃ ገዢነት ሹመት ሲሰጥ ለሌሎች ደግሞ የክፍለሃገር ከተማ ከንቲባነት እና በሞስኮ ከተማ አታሼነት ተሰጠ። ሌሎቹ ያለምንም ማንገራገር ሹመቱን ሲቀበሉ መስፍን ግን ስለሹመቱ ከንጉሱ ማብራሪያ ካላገኙ እንደማይሄዱ ተናገሩ። የአክሊሉ ካቢኔም "ሹመቱ የተሰጠህ ከመተቸት ውጭ የተሻለ አስተዳደር ታመጣ እንደሆነ እንድታሳይን ነው" አላቸው። ሲመልሱም "በአውሮፕላን ስሄድ አየር ላይ መናጥ ሲበዛብኝ አስተናጋጁን ምነው መናጥ በዛ ስለው መልሱ ከቻልክ የማብረሪያው ክፍል (cockpit) ግባና አውሮፕላኑን አብረው ሊሆን አይገባም።" ሲሉ የአካዳሚክ ነጻነቱን ተጠቅሞ በሚያስተምር ምሁር ላይ አጸፋዊ እርምጃ መወሰድ እንደሌለበት አስረዱ።ለዚህ ጠንካራ አቋማቸውም ጥቂት ቀናት ሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ





እንዲከርሙ ሆነ። (Professor Mesfin Woldemariam, PM Meles Zenawi and Ethiopia by Negussay Ayele,September 6,2006) ይህንን የፕሮፌሰር መስፍንን የአካዳሚክ ነፃነትን የማስከበር ፅኑ አቋም "የማስተዳደር ሥራ ስለማይችል ነው ሹመቱን ያልተቀበለው" በሚል ስማቸውን የሚያጠፉ የእድሜ እኩዮቻቸው አጋጥመውኛል። በደርግ ጊዜ በመርማሪ ኮሚሲዮኑ ተመርጠው ለጥቂት ጊዜ በመስራታቸው የተነሳ ስድሳዎቹን እንዳስረሸኑ አድርገው የሚያስወሩ ስራፊቶችና ይህንኑ የሚያምኑ ጅሎች እስከዛሬ መኖራቸውንም ታዝቤያለሁ። የደርግ ዋና ሰዎች መንግስቱ ኃ/ማርያምንም ጨምሮ እስከዛሬ ድረስ ሳይገድሏቸው በመውደቃቸው እንዲሁ ስማቸውን ለማጥፋት እንደባጁ አሉ። ግን በወያኔ የውሸት ፍርድ ቤት ለማስመሰል እንኳ የሚበቃ ቅንጣት ማስረጃ ስለሌለ መንግስቱም ሟቹ መለስም አንዳቸው የወያኔ ሰው ነው ሌላኛቸው ደግሞ የደርግ ሰው ነው ብለው ስማቸውን ከሚያጠፉ በቀር የፕሮፌሰር መስፍን የረጅም ዘመን ታሪክ ላይ ጉድፍ ማግኘት አልተቻለም።የዘውዱን ሥርዓት እቃወማለሁ ይል የነበረውና ራሱን በግራ የፈረጀው የተማሪው እንቅስቃሴም ወደብረት የአመፅ ትግል ሲያዘነብል ሃሳብ ለሃሳብ ብቻ የሚፋጭበት የአካዳሚክ ሕይወትና ጡንቻ አብረው አይሄዱም በማለት ፕሮፌሰሩ ስለተቃወሙ ከዚህ ጮርቃነት እስከዛሬ ያልወጡት ስማቸውን እንዳብጠለጠሉት አሉ። እናም ይቺ በታምራትም ፕሮፌሰሩን የ"ቀኝ ዘመም ፖለቲካ ጠላ ጠማቂ" የማድረግ ነገር ምንጯ ከዚህ የተለየ አይደለም። ባጭሩ ፕሮፌሰሩ በፅኑ አቋማቸው የተነሳ ቀኝ ተብለው የተፈረጁበት ሁኔታ "ግራ ዘመም" ነኝ የሚለውን ኢትዮጵያዊ የዘውትር ክሽፈት የሚያሳይ ዝብዛንኬ ነው። ታምራት "ባንድም ሆነ በሌላም መልኩ ስለመክሸፍ የኢትዮጵያ ምሁራን አውርተዋል" ሲል በተማሪዎች ረብሸኝነት በጎሳ ነጻ አውጪነት እና የጎሳ ማህበራት ተሰባስበው ራሳቸውን የሽግግር መንግስት ስላሉበት ሁኔታ አለመሳካት የጻፉትን ከመስፍን የመክሸፍ ትንተና ጋር ማያያዙ አንዱ ከመጽሐፉ በኋላም እንኳ እንዴት መክሸፍ እንዳላባራ ማሳያ ነው። ታምራት የጠቀሳቸው ምሁራን ባአብዛኛው ከሽፎ ስላከሸፈ

ትውልድ መክሸፍን እንደሚፈልገው አድርጎ እንዲቀጥል ባለማድረጉ ስላለው ክሽፈት ካልሆነ በቀር ስለኢትዮጵያ ታሪክ ክሽፈት ጻፉ፣ተመራመሩ ለማለት አይቻልም። እነዚህ በአብዛኛው ራሱ ታምራት ለሚለው የ"ምናባዊት ኢትዮጵያ ማኅበረሰብ" አለመፈጠር ምክንያት ሆነው ክሽፈው ያክሸፉ ናቸው።እንዴት ሆኖ በእኔ ሞት የኢሕአዴግ የሽግግር መንግስት ክሽፈት ከኢትዮጵያ መክሸፍ ትንተና ጋር የሚያያዘው።ኢሕአዴግ የሚባለው መጥፎ ወንበሩ ላይ ሲቀመጥ የኢትዮጵያ መክሸፍ የለየለት ሁኔታ ነው የተፈጠረው። ኦነግ እና ወያኔ ሽግግር በሚባለው ዘመን ተጣልተው በየፊናቸው ባይሄዱ ኖሮ ክሽፈት አይኖርም ነበር ለማለት ከሆነ ከባድ ቧልት ነው።

ታምራት "ስለኢትዮጵያ ሲባል ለምን ሐበሻ ልቡ ይፈሳል?" ሲል የጠየቀውን ጥያቄ ኢትዮጵዊነት ገብቶት ነው ብዬ ባስብ ኖሮ እወድለት ነበር። አንዱ የሐበሻን ልብ የሚያፈሰው እንደዚህ እሱ እንደጻፈው ያለ የተሳከረ ጽሑፍ መሆኑን ልነግረው እወዳለሁ። አገር ወዳድነት ሌላ ቦታ የለውም ከመንደርተኝነት መውጣት ነው። ከመንደርተኝነት የወጣ ሰው ስለአገር ወዳድነት ማብራራት የግድ ካለበት እንደሩሲያዊው ሌርሞንቶቭ "I love my country, but with a strange love. My reason cannot fathom it." ማለት ብቻ ይበቃዋል። ሌላው ሃተታ በማያንሰራራ ሁኔታ ይበልጥ እንድንከሽፍ ማጨናበር ነው።





# ምዕራፍ ፱
# የትችቶች ትችት

*መግቢያ*

ስለትችቶቹ መናገር ግዴታ መስሎ ስለታየኝ ነው እንጂ ፍላጎቱ የለኝም፤ በመሠረቱ በአንድ መጽሐፍ ላይ ትችት ለመስጠት ብቃቱ ያላቸው ሰዎች ደረሲውንም አንባቢውንም ለማስተማር የሚችሉ ናቸው፤ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የሚታየው ግን ፊደል የቆጠረ ሁሉ ማንኛውንም መጽሐፍ ለመተቸትና ከሱ ባልተሻሉ አድናቂዎቹ ‹‹አበጀህ የኛ ልጅ!›› ለመባል የሚጠብቅ ሞልቷል፤ እነዚህ ሰዎች የሚተቹትን መጽሐፍ በጥንቃቄ ማንበብ አይጠበቅባቸውም፤ ያልታደሉት አድናቂዎቻቸው ምንም ነገር ቢወረውሩላቸው እልል እያሉ የሚቀበሉ ናቸው፤ እነዚህን ወጣቶች ለእነዚህ ሰዎች መተው ትክክል አይመስለኝምና ያንን በመጠኑም ቢሆን ለመቋቋም ይጠቅማል በማለት ነው፤ አንዳንዶች ተቺዎች በቅድሚያ የእኔን ጠባይ በማጥላላት እነሱ ለራሳቸው ተአማኒነት ለማግኘት ይጥራሉ፤ ምናልባትም በቅድሚያ ማከላከያቸውን ማዘጋጀታቸው ይሆናል፤ እኔ ትችቶችን መቀበል መቻሌን ለማሳየት አንድ የቆየ ምሳሌ በማስረጃነት አቀርባለሁ፤ ሆኖም የእኔ ትችትን መቀበል ወይም አለመቀበል ዋጋ የለውም፤ ትችቱ የማይረባ ከሆነ ይበልጥ የሚጎዳው ማኅበረሰቡን ነው።

በ1966 ዓ.ም. አንድ ትንሽ ጽሑፍ ኢትዮጵያዊነት፤-ልማት በኅብረት በሚል ርእስ አሳትሜ ነበር፤ ዓላማዩ አብዮት የሚባለው ጎርፍ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደጥፋት እየመራው